**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት**

**ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ**

**DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA**

**OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE**

፩ኛ ዓመት ቁጥር 1
አርባ ምንጭ ነሐሴ 03 ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No 1
Arba minch 19th August, 2023

| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| **አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፮** | **Proclamation No. 1/2023** |
| **የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት  አዋጅ--- ገፅ** | **Proclamation of the Constitution of the South Ethiopia Regional State---Page 1** |
| **አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፮** | **Proclamation No. 1/2023** |
| **<u>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት  ሕገ መንግሥት ሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ</u>** | **A Proclamation to Pronounce the Coming into Effect of the Constitution of the South Ethiopia Regional State** |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ወክለው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ነሐሴ 02 ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥትን በማጽደቃቸው የሚከተለው ታውጇል፡፡ | WHEREAS, the Nation, Nationalities and Peoples of the South Ethiopia Region have, through their elected representatives, ratified the Constitution of the South Ethiopia Regional State, on the 18th  day of August 2023; it is hereby proclaimed as follows; |
| | |

| | |
|---|---|
| **1. አጭር ርዕስ** | **1. Short Title** |
| ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ | This proclamation may be cited as the "Constitution of the South Ethiopia Regional State Proclamation No. 1/2023". |
| **2. ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ ስለመዋሉ** | **2. Coming into Effect of the Constitution** |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥት ከነሐሴ 03 ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ | The Constitution of the Southe Ethiopia Region has come into full force and effect as of the 19th day of August, 2023. |
| **3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ** | **3. Effective Date** |
| ይህ አዋጅ ከነሐሴ 03 ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ | This Proclamation shall enter into force as of the 19th day of August, 2023. |
| **አርባ ምንጭ ነሐሴ 03 ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም** | **Done at Arba minch,this 19th day of August 2023** |
| **ጥላሁን ከበደ** | **Tilahun Kebede** |
| **የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር** | **CHIEF EXECUTIVE OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE** |
| **መግቢያ** | |

| | |
|---|---|
| | **PREAMBLE** |
| እኛ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፡- | We, the Nations, Nationalities and Peoples of the South Ethiopia Region:- |
| የጋራና የየራሳችን የሆነ አኩሪ ባሕልና ታሪክ ያለን፤ የየራሳችን መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የምንኖር በመሆኑ፤ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት፤ የሥነ ልቦና አንድነትና የመልማት ፍላጎት አለን ብለን ስለምናምን፤ | Convinced that by continuing to live with our common and unique proud cultural and historical legasies in territories we have long inhabited, we have through continuous interaction on various forms and levels , built up common interest and outlooks, psychological unity and a desire to develop; |
| ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነፃነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ ፍላጎታችን በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ክልል በጋራ መመሥረት አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤ | Believed that, in full and free exercise of our right to self-determination, to establishing a region based on the rule of law and our own will is necessary in order to create sustainable and mutually supportive conditions for ensuring respect for our rights and freedoms, and for the collective promotion of our interests; |
| በጋራ መፈቃቀድና እኩልነት ላይ ተመስርተን ባቋቋምነው ክልላችን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፤ ማንነታችን ተከብሮ ቋንቋችንን፣ ባሕላችንና አንድነታችንን ይበልጥ ለማጠናከር እና ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ እንዲሁም ሀገራችን አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመገንባት በምታደርገዉ ጥረት ውስጥ የበኩላችንን ሚና ለመወጣት የሚያስችለን ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መመስረት አስፈላጊ መሆኑን አጥብቀን በማመን፤ | Strongly believed that it is necessary to establish a constitutional system that would allow us to ensure the supremacy of the law, to advance our economic and social development, to further develop our language, culture and unity, and consolidate as a lasting legacy, the peace and the prospect of a democratic order. as well as to play our part in our country's efforts to build one economic and political society in a Region we have established on the basis of equality and common understanding ; |
| በክልሉ ቀጣዩ የጋራ ጥቅማችንንና እድገታችን መመሥረት ያለበት የዜጎችንና የማኅበረሰብ ብዝሃነት፣ አብሮነት፤ የመቻቻልና የመከባበር እሴትን መሰረት በማድረግ እና ዘላቂ ሰላምና እድገት በማረጋገጥ እንዲሁም ያለንን የሰው እና ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብትን ለጋራ እድገትና ጥቅም ለማዋል የተሻለ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት መገንባት አስፈላጊ መሆኑን በመቀበል፤ | |
| በክልላችን መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ የአገልግሎት | |

ተደራሽነትን በማረጋገጥ፣ በእኩልነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እና ግልፅ አሠራርንና የሥልጣን ክፍፍል ላይ የተመሰረተ የመንግሥት አካላት አደረጃጀትን እውን ማድረግ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ ፈጣን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣትና ለጋራ እድገታችን ያለውን ጠቄሜታ በመገንዘብና በውል በመረዳት፤

በክልላችን ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ እንዲሁም የግለሰብ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን ማክበር፣ የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ፣ ቋንቋዎችንና ባሕሎችን እኩል ማሳደግ፣ እምነቶችንና ሃይማኖቶችን ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ ማድረግ ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤

ይህንን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥት ከዚህ በላይ ለገለጽናቸዉ ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በሕገ መንግሥት አጽዳቂ ጉባዔ ዛሬ ነሐሴ 02 ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም አጽድቀነዋል፡፡

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 1</u>**

**<u>የክልሉ መንግሥት መቋቋም እና ስያሜ</u>**

ይህ ሕገ መንግሥት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት የተቋቋመው መንግሥት “የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ

Cognizant that our future common interest and development in the Region can best be served by respecting the values of diversity, solidarity and tolerance of citizens and society, and by ensuring sustainable peace and growth, as well as by building a better governmental administration system to use our human and natural resources for common development and benefit;

Recognized that it would be beneficial to accelerat our mutual development, to bring rapid social and economic growth to the region and the country is realized only by establishing good governance, and by ensuring access to services, by organizing government bodies structures based on equality and fair use on transparent operation and distribution of power in the region;

Firmly convinced that the fulfillment of these objectives in our State requires full respect of individual and Nations. Nationalities and People’s fundamental rights and freedoms, recognition of the equality of sex, languages, and religions without any discrimination;

Now, therefore, approved, on 18 August, 2023 this constitution of the South Ethiopia Region through representatives we have duly elected for this purpose as an instrument that binds us in a mutual commitment to fulfill the objectives and the principles set forth above.

መንግሥት” በሚል ስም ይጠራል፡፡

**አንቀጽ 2**

**የክልሉ ግዛት እና አስተዳደር ወሰን**

በፌዴራሉ መንግሥት ሕገ መንግሥት የተመለከተው የግዛት ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አስተዳደር ወሰን በክልሉ የሚገኙ ዞኖች፤ ከሌሎች አጎራባች ክልሎች ጋር ያላቸው ወሰን እና ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላት ድንበር ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 3**

**የክልሉ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ**

1 የክልሉ ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ፤ ከመሐል ውሃ ሰማያዊ፤ ከታች ቀይ ሆኖ በአግድም የተቀመጡ ሲሆን ከአረንጓዴው እና ከቀዩ ቀለም መስቀያ ጠርዞች በመነሳት ሰማያዊው መደብ ላይ የሚያርፍ ሦስት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ቢጫ ቀለም ሆኖ በመሐሉ በሚገኘዉ ውሃ ሰማያዊ መደብ ላይ የክልሉ ዓርማ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ቀለማት በጥቁር መስመሮች ተለያይተዋል፡፡

2 በሰንደቅ ዓላማዉ ውሃ ሰማያዊ መደብ መሃል ላይ የሚቀመጠው ዓርማ ክልሉ የሠላም፤ የመቻቻልና የብልፅግና ተምሳሌት መሆኑን፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል፡፡

3 የሰንደቅ ዓላማውና የዓርማው ዝርዝር የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 4**

**CHAPTER ONE**

**GENERAL PROVISIONS**

**Article 1**

**Establishment and Nomenclature of the Regional State**

This Constitution proclaims the Democratic structure of the South Ethiopia Regional State. Accordingly, the state established shall be known as the "South Ethiopia Regional State"

**Article 2**

**Territorial Boundaries of the State**

Without Prejudice to the boundaries stated in the Constitution of the Federal Government, the boundaries of the Regional State shall be the administrative territories of the respective zones with other regions, and Ethiopia’s boundary with neighboring country.

**Article 3**

**Flag and Emblem of the State**

1. The State flag shall consist of the green at top,

**የክልሉ መዝሙር**

የክልሉ መዝሙር በክልሉ የሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሏቸዉን ተፈጥሮአዊ ገፀ በረከቶች፣ እሴቶች፣ ለመልማት ያላቸውን ብሩህ ተስፋ፣ ስለሀገር ሉዓላዊነት የከፈሉትን መስዋዕትነት፣ በክልሉ ሕዝቦች መካከል ያለዉን ማኅበራዊ መስተጋብር እና ክልሉ ለሀገር አንድነት ያለውን አስተዋጽኦ የሚገልጽ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 5**

**ቋንቋ**

1 በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግሥት ዘንድ እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፡፡

2 አማርኛ የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡

3 በክልሉ የሚገኙ ዞኖች በየምክር ቤቶቻቸው የየራሳቸውን የሥራ ቋንቋ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 6**

**ርዕሰ ከተማ**

1 የክልሉ መንግሥት እኩል ደረጃ ያላቸው ብዝሀ ርዕሰ ከተሞች ይኖሩታል፡፡ እነሱም ዎላይታ ሶዶ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ጂንካ፣ ሳውላ እና ካራት ናቸው፡፡

2 የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መቀመጫ ዎላይታ ሶዶ ይሆናል፡፡

water blue in the middle, red at the bottom placed horizontally, and shall begin from the edges of the green and red colors; a triangular yellow color rests on the blue layer, and shall have a State emblem at the center. Each color shall be separated by black lines.

2. The Regional State emblem on the flag shall reflect the hope of the Nations, Nationalities, and Peoples of the Region to live together in equality and unity, and it symbolizes peace, tolerance and prosperity of the Region.
3. Details of the flag and the emblem shall be determined by law of the State Council.

**Article 4**

**The State Anthem**

The State anthem, to be determined by law, shall refelect natural blessings, values, heroism, prospect of development, the sacrifices made for the sovereignty of the country by the people of the region, the interaction between the peoples of the region and the contribution of the region to the national unity.

3 የክልል ማዕከል ከተሞች ተጠሪነትና አስተዳደራዊ ጉዳይ የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ 7</u>**

**<u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የሕገ መንግሥቱ መሰረታዊ መርሆዎች</u>**

**<u>አንቀጽ 8</u>**

**<u>የሕዝብ ሉዓላዊነት</u>**

1 የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልሉ መንግሥት ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት ናቸው፡፡

2 ይህ ሕገ መንግሥት የሉዓላዊነታቸው መገለጫ ነው፡፡

3 ሉዓላዊነታቸውም የሚገለጸው በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸው እና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 9</u>**

**<u>የሕገ መንግሥት የበላይነት</u>**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ

**Article 5**

**Language**

1. All Languages in the Region shall enjoy equal State recognition.
2. Amharic shall be the working language of the Regional State.
3. Zones in the region may determine their respective working language in their own Councils.

**Article 6**

**Capital City**

1. The Regional state shall have multi capital city with equal status. They are Wolaita Sodo, Arba Minch, Dilla, Jinka, Sawula and Karat.
2. Wolaita Sodo shall be the seat of the Chief Executive of the region.
3. Accountability and administrative affairs of the Capital Cities shall be determined by the law issued by the State Council.

**Article 7**

**Gender Expression**

መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1 ይህ ሕገ መንግሥት በክልሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2 ማንኛውም ሰው፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ይህንን ሕገ መንግሥት የማክበር፣ የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3 በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በሌላ መንገድ የመንግሥትን ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ 0

## ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

1 ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰዉ ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡

2 በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 01

## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1 መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡

2 መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡

3 መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

Provisions of this Constitution set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

# CHAPTER TWO

# THE FUNDAMENTAL PRINCIPLES OF THE CONSTITUTION

## Article 8

## Sovereignty of the People

1. All sovereign power of the Regional State resides in the Nations, Nationalities and Peoples of Regional State.
2. This Constitution is an expression of their sovereignty.
3. Their sovereignty shall be expressed through their representatives elected in accordance with this Constitution and through their direct democratic participation their elected representatives according to this constitution.

## Article9

## Supremacy of the Constitution

Without Prejudice to the supremacy of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia:

1. This Constitution is the supreme law of the

ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

**<u>አንቀጽ 02</u>**

**<u>የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት</u>**

1 የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡

2 ማንኛውም ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነት ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3 ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**

**<u>መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች</u>**

**<u>አንቀጽ 03</u>**

**<u>ተፈጻሚነትና አተረጓጎም</u>**

1 በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ፣ የሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡

2 በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ጋር

Regional State. Any law, customary practice or a decision of an organ of state or a public official which contravenes this Constitution shall be of no effect.

2. All citizens, organs of state, political organizations, other associations as well as their officials have the duty to ensure observance of the Constitution and to obey it.

3. It is prohibited to assume state power in any manner other than that provided under the Constitution.

**Article 10**

**Human and Democratic Rights**

1. Human rights and freedoms, emanating from the nature of mankind, are inviolable and inalienable.
2. Human and democratic rights of citizens and peoples shall be respected.

**Article 11**

**Separation of State And Religion**

1. State and religion are separate.
2. There shall be no state religion.
3. The State shall not interfere in religious matters and

በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ፡፡

**ክፍል አንድ**

**ሰብዓዊ መብቶች**

**አንቀጽ 04**

**የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት**

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 05**

**የሕይወት መብት**

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

**አንቀጽ 06**

**የአካል ደህንነት መብት**

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 07**

**የነፃነት መብት**

1 በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነፃነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡

religion shall not interfere in state affairs.

**Article 12**

**Conduct and Accountability of State**

1. The conduct of affairs of the Regional government shall be transparent
2. Any public official or an elected representative is accountable for any failure in official duties.
3. An elected representative may be recalled if the electorate lack confidence in him. Particulars shall be determined by law.

## CHAPTER THREE

## FUNDAMENTAL RIGHTS AND FREEDOMS

**Article 13**

**Applicability and Interpretation**

1. All State legislative, executive and judicial organs at all levels shall have the responsibility and duty to respect and enforce the provisions of this Chapter.
2. The fundamental rights and freedoms specified in this Chapter shall be interpreted in a manner conforming to the principles of the Universal Declaration of Human Rights, International

2 ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

**<u>አንቀጽ 08</u>**

**<u>ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ</u>**

1 ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

2 ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡

3 ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት" የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፤

ሀ) ማንኛውም እስረኛ በእሥራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሰረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ) ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን ማንኛውም አገልግሎት፣

ሐ) የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውንም አገልግሎት፣

መ) በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው

Covenants on Human Rights and International instruments adopted by Ethiopia.

**PART ONE**

**HUMAN RIGHTS**

**Article 14**

**The Right to life, the Security of Person and Liberty**

Every person has the inviolable and inalienable right to life, security of person and liberty.

**Article 15**

**Right to Life**

Every person has the right to life. No person may be deprived of his life except as a punishment for a serious criminal offence determined by law.

**Article 16**

**The Right of the Security of Person**

Every one has the right to protection against bodily harm.

**Article 17**

የሚፈጸመውን ማንኛውም ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ የልማት ሥራ፡፡

**<u>አንቀጽ 09</u>**

**<u>የተያዙ ሰዎች መብት</u>**

1 ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው፡፡

2 የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፣ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው፡፡

3 የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው፡፡

4 የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ፣ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ስር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች

**Right to Liberty**

1. No one shall be deprived of his liberty except on such grounds and in accordance with such procedure as are established by law.
2. No person shall be subjected to arbitrary arrest, and be detained without a charge or conviction.

**Article 18**

**Prohibition Against Inhuman Treatment**

1. Everyone has the right to protection against cruel, inhuman or degrading treatment or punishment.
2. No one shall be held in slavery or servitude. Trafficking in human beings for whatever purpose is prohibited.
3. No one shall be required to perform forced or compulsory labour.
4. For the purpose of sub-Article 3 of this Article, the phrase "forced or compulsory labour" shall not include: -
   a. Any work or service normally required of a person who is under detention in consequence of a lawful order, or of a person during conditional release from such

ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት፡፡

5 የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6 የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፳</u>**

**<u>የተከሰሱ ሰዎች መብት</u>**

1 የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡

2 ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3 በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡

4 የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ

detention;

b. In the case of conscientious objectors, any service exacted in lieu of compulsory military service;

c. Any service exacted in cases of emergency or calamity threatening the life or well-being of the community;

d. Any economic and social development activity voluntarily performed by a community within its locality.

**Article 19**

**Right of Persons Arrested**

1. Persons arrested have the right to be informed promptly, in a language they understand, of the reasons for their arrest and of any charge against them.
2. Persons arrested have the right to remain silent. Upon arrest, they have the right to be informed promptly, in a language they understand, that any statement they make may be used as evidence against them in court.
3. Persons arrested have the right to be brought before a court within 48 hours of their arrest. Such time shall not include the time reasonably required for the journey from the place of arrest to the court. On

እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

5 በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

6 ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

7 የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ፳1

### በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1 በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡

2 ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ፳2

### የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለመሆኑ

1 ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት

appearing before a court, they have the right to be given prompt and specific explanation of the reasons for their arrest due to the alleged crime committed.

4. All persons have an inalienable right to petition the court to order their physical release where the arresting police officer or the law enforcer fails to bring them before a court within the prescribed time and to provide reasons for their arrest.Where the interest of justice requires, the court may order the arrested person to remain in custody or, when requested remand him for a time strictly required to carry out the necessary investigation. In determining the additional time necessary for investigation, the court shall ensure that the responsible law enforcement authorities carry out the investigation respecting the arrested person's right to a speedy trial.

5. Persons arrested shall not be compelled to make confessions or admissions which could be used in evidence against them. Any evidence obtained under coercion shall not be admissible.

6. Persons arrested have the right to be released on bail. In exceptional Circumstances prescribed by law, the court may deny bail or demand adequate guarantee for the conditional release of the arrested

ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም፡፡

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ፳3

## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

## አንቀጽ ፳4

## የክብርና የመልካም ስም መብት

1 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፡፡

2 ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው፡፡

3 ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ ፳5

person.

## Article 20

## Rights of Persons Accused

1. Accused persons have the right to a public trial by an ordinary court of law within a reasonable time after having been charged. The court may hear cases in a closed session only with a view to protecting the right to privacy of the parties concerned, public morals and national security.
2. Accused persons have the right to be informed with sufficient particulars of the charge brought against them and to be given the charge in writing.
3. During proceedings accused persons have the right to be presumed innocent until proved guilty according to law and not to be compelled to testify against themselves.
4. Accused persons have the right to full access to any evidence presented against them, to examine witnesses testifying against them, to adduce or to have evidence produced in their own defense, and to obtain the attendance of and examination of witnesses on their behalf before the court.
5. Accused persons have the right to be represented by legal counsel of their choice, and, if they do not have sufficient means to pay for it and miscarriage of justice would result, to be provided with legal representation at state expense.
6. All persons have the right of appeal to the

**የእኩልነት መብት**

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ ፳6**

**የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት**

1 ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ፣ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡

2 ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡

3 የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብ ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጎች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

competent court against an order or a judgment of the court which first heard the case.

7. They have the right to request for the assistance of an interpreter at state expense where the court proceedings are conducted in a language they do not understand.

**Article 21**

**The Rights of Persons Held in Custody and Convicted Prisoners**

1. All persons held in custody and persons imprisoned upon conviction and sentencing have the right to treatments respecting their human dignity.
2. All persons shall have the opportunity to communicate with, and to be visited by, their spouses or partners, close relatives, friends, religious councilors, medical doctors and their legal counsel.

**Article 22**

**Non-retroactivity of Criminal Law**

1. No one shall be held guilty of any criminal offence on account of any act or omission which did not constitute a criminal offence at the time when it was committed. Nor shall a heavier penalty be imposed on any person than the one that was applicable at the time when the criminal offence

**አንቀጽ ፳7**

**የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት**

1 ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡

2 በአንቀጽ ፪፷1 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የማያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

3 ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡

4 ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡

5 ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶች፣ እና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፳8**

**በሰብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች**

was committed.

2. Notwithstanding the provisions of sub-Article 1 of this Article, a law promulgated subsequent to the commission of the offence shall apply if it is advantageous to the accused or convicted person.

**Article 23**

**Prohibition of Double Jeopardy**

No person shall be liable to be tried or punished again for an offense for which he has already been finally convicted or acquitted in accordance with the criminal law and procedure.

**Article 24**

**Right to Honour and Reputation**

1. Everyone has the right to respect for his human dignity, reputation and honour.
2. Everyone has the right to the free development of his personality in a manner compatible with the rights of other citizens.
3. Everyone has the right to recognition every where as a person.

**Article 25**

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፡ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>ዴሞክራሲያዊ መብቶች</u>**

**<u>አንቀጽ ፳9</u>**

**<u>የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት</u>**

1 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡

2 ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል፡፡

3 የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡

ሀ) የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

ለ) የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት

**Right to Equality**

All persons are equal before the law and are entitled without any discrimination to the equal protection of the law. In this respect, the law shall guarantee to all persons equal and effective protection without discrimination on grounds of race, nation, nationality, or other social origin, colour, sex, language, religion, political or other opinion, property, birth or other status.

**Article 26**

**Right to Privacy**

1. Everyone has the right to privacy. This right shall include the right not to be subjected to searches of his home, person or property, or the seizure of any property under his personal possession.

2. Everyone has the right to the inviolability of his notes and correspondence including postal letters, and communications made by means of telephone, telecommunications and electronic devices.

3. Goverenment officials shall respect and protect these rights. No restrictions may be placed on the enjoyment of such rights except in compelling circumstances and in accordance with specific laws

ዕድልን፡፡

4 ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

5 በክልሉ መንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በክልሉ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

6 እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናሉ፡፡

7 ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፴</u>**

**<u>የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>**

1 ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ

whose purposes shall be the safeguarding of national security or public peace, the prevention of crimes or the protection of health, public morality or the rights and freedoms of others.

**Article 27**

**Freedom of Religion, Belief and Opinion**

1. Everyone has the right to freedom of thought, conscience and religion. This right shall include the freedom to hold or to adopt a religion or belief of his choice, and the freedom, either individually or in community with others, and in public or private, to manifest his religion or belief in worship, observance, practice and teaching.
2. Without prejudice to the provisions of sub-Article 2 of Article 121, believers may establish institutions of religious education and administration in order to propagate and organize their religion.
3. No one shall be subject to coercion or other means which would restrict or prevent his freedom to hold a belief of his choice.
4. Parents and legal guardians have the right to bring up their children ensuring their religious and moral

ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡

2 ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡፡

**<u>አንቀጽ ፴1</u>**

**<u>የመደራጀት መብት</u>**

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፴2</u>**

**<u>የመዘዋወር ነፃነት እና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ

education in conformity with their own convictions.

5. Freedom to express or manifest one’s religion or belief may be subject only to such limitations as are prescribed by law and are necessary to protect public safety, peace, health, education, public morality or the fundamental rights and freedoms of others, and to ensure the independence of the state from religion.

**Article 28**

**Crimes Against Humanity**

Criminal liability of persons who commit crimes against humanity, so defined by international agreements ratified by Ethiopia and by other laws of Ethiopia, such as genocide, summary executions, forcible disappearances or torture shall not be barred by statute of limitation. Such offences may not be commuted by amnesty or pardon of the legislature or any other state organ.

## PART TWO

## DEMOCRATIC RIGHTS

**Article 29**

**Right of Thought, Opinion and Expression**

ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠዉ የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣ የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሰርቶ የመኖር፣ ሀብትና ንብረት የማፍራት እና የመያዝ፣ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለዉ፡፡

**አንቀጽ ፴3**

**በሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች የመሳተፍ መብት**

የክልሉን ወይም የዞኑን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጲያዊ በማንኛውም የክልሉ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች ተመርጦ ወይም ተመድቦ የመሥራት መብት አለው፡፡

**አንቀጽ ፴4**

**የጋብቻ፤ የግልና የቤተሰብ መብቶች**

1 በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ ወይም በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነግጋሉ፡፡

2 ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡

3 ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

4 በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሃይማኖት፣ በባሕል

1. Everyone has the right to hold opinions without interference.
2. Everyone has the right to freedom of expression without any interference. This right shall include freedom to seek, receive and impart information and ideas of all kinds, regardless of frontiers, either orally, in writing or in print, in the form of art, or through any media of his choice.
3. Freedom of the press and other mass media and freedom of artistic creativity is guaranteed. Freedom of the press shall specifically include the following elements:
   a. Prohibition of any form of censorship.
   b. Access to information of public interest.
4. In the interest of the free flow of information, ideas and opinions which are essential to the functioning of a democratic order, the press shall, as an institution, enjoy legal protection to ensure its operational independence and its capacity to entertain diverse opinions.
5. Any media in the Regional State financed by or under the control of the Regional State shall be

ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡

5 ይህ ሕገ መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕላዊ ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፴5</u>**

**<u>የሴቶች መብት</u>**

1 ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

2 ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

3 ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡

4 ሴቶች ከጎጂ ልማድ ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡

5 ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ እድገት፤ የእኩል ክፍያና ጡረታን

operated in a manner ensuring its capacity to entertain diversity in the expression of opinion.

6. These rights can be limited only through laws which are guided by the principle that freedom of expression and information cannot be limited on account of the content or effect of the point of view expressed. Legal limitations can be laid down in order to protect the well-being of the youth, and the honour and reputation of individuals. Any propaganda for war as well as the public expression of opinion intended to injure human dignity shall be prohibited by law.

7. Any citizen who violates any legal limitations on the exercise of these rights may be held liable under the law.

**Article 30**

**The Right of Assembly, Demonstration and Petition**

1. Everyone has the right to assemble and to demonstrate together with others peaceably and unarmed, and to petition. Appropriate regulations may be made in the interest of public convenience relating to the location of open-air meetings and the route of movement of demonstrators or, for the protection of democratic rights, public morality and peace during such a meeting or demonstration.

የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡

6 በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች፡-

ሀ) የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

ለ) የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡

7 ሴቶች በክልላዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፡ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

8 ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡

9 ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

2. This right does not exempt from liability under laws enacted to protect the well-being of the youth or the honour and reputation of individuals, and laws prohibiting any propaganda for war and any public expression of opinions intended to injure human dignity.

## Article 31

## Freedom of Association

Every person has the right to freedom of association for any cause or purpose. Organizations formed, in violation of appropriate laws, or to illegally subvert the constitutional order, or which promote such activities are prohibited.

## Article 32

## Freedom of Movement and the Right to Establish Residence

Without prejudice to the provisions of Article 32, of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, any resident of the region or person found therein in a legal way, has the right to freedom of

## አንቀጽ ፴6

## የሕፃናት መብት

1 ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

ሀ) በሕይወት የመኖር፣

ለ) ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ) ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ) ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠሩ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ) በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፡፡

2 ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡

3 ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ

movement and establish place of abode in any area of his choice inside the regional state, live with gainful occupation, produce and thereby possess wealth and property as well as leave the region any time he wishes to.

## Article 33

## The Right to Engage in Public and Goverenmental Occupations

Any Ethiopian who speakes the working language of the Region or the Zone has the right to be assigned or elected to serve in governmental and social activites of the State or the Zone.

## Article 34

## Marital, Personal and Family Rights

1. .Men and women, without any distinction as to race, nation, nationality or religion, who have attained marriageable age as defined by law, have the right to marry and found a family. They have equal rights while entering into, during marriage and at the time of divorce. Laws shall be enacted to ensure the protection of rights and interests of children at the time of divorce.
2. Marriage shall be entered into only with the free and full consent of the intending spouses.
3. The family is the natural and fundamental unit of society and is entitled to protection by society and

አለባቸው፡፡

4 ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

5 መንግሥት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል፡፡

## አንቀጽ ፴7

## ፍትሕ የማግኘት መብት

1 ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፣

ሀ) ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ) ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ ፴8

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ

the State.

4. In accordance with provisions to be specified by law, a law giving recognition to marriage concluded under systems of religious or customary laws may be enacted.
5. This Constitution shall not preclude the adjudication of disputes relating to personal and family laws in accordance with religious or customary laws, with the consent of the parties to the dispute. Particulars shall be determined by law.

## Article 35

## Rights of Women

1. Women shall, in the enjoyment of rights and protections provided for by this Constitution, have equal right with men.
2. Women have equal rights with men in marriage as prescribed by this Constitution.
3. The historical legacy of inequality and discrimination suffered by women in Ethiopia taken into account, women, in order to remedy this legacy, are entitled to affirmative measures. The purpose of such measures shall be to provide special attention to women so as to enable them to compete and participate on the basis of equality with men in political, social and economic life as well as in public and private institutions.

ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

ሀ) በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣

ለ) ዕድሜው 08 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥና ዕድሜው ፳1 ሲሞላ ደግሞ የመመረጥ መብት አለው፡፡

ሐ) በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፡፡ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

2 በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ በኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ፡፡

4 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ ፴9**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት**

ማንኛውም የክልሉ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ በኢትዮጵያ

4. The State shall enforce the right of women to eliminate the influences of harmful customs. Laws, customs and practices that oppress or cause bodily or mental harm to women are prohibited.

5. Women shall have a right to equality in employment, promotion, payment, and the transfer of pension entitlements.

6. Women employed in government offices or private organizations:

   a. Have the right to maternity leave with full pay. The duration of maternity leave shall be determined by law taking into account the nature of the work, the health of the mother and the well-being of the child and family.

   b. Maternity leave may, in accordance with the provisions of law, include prenatal leave with full pay.

7. Women have the right to full consultation in the formulation of Regional state development policies, the designing and execution of projects, and particularly in the case of projects affecting the interests of women.

8. Women have the right to acquire, administer, control, use and transfer property. In particular, they have equal rights with men with respect to use,

ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ማንኛውም የክልሉ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ፡-

1 የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርስንና ታሪክን የመንከባከብና የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ ቋንቋውን የማሳደግ፣ ባሕሉን የመግለጽ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው፣

2 በራስ መልከዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ውስጥ በነፃነት፣ ተገቢና ፍትሀዊ በሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ የማድረግ መብት አለው፣

3 የራሱን የማስተዳደር መበት፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልከዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና እንዲሁም በክልልና በፌዴራል መንግሥት አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፣

4 የክልሉ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለ መብት በሥራ ላይ የሚዉለው፡-

ሀ) የመገንጠል ጥያቄ በብሔር፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

ለ) የፌዴራሉ መንግሥት የብሔር፣ የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት የመገጠል ውሳኔው በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

transfer, administration and control of land. They shall also enjoy equal treatment in the inheritance of property.

9. To prevent harm arising from pregnancy and childbirth and in order to safeguard their health, women have the right of access to family planning education, information and capacity.

**Article 36**

**Rights of Children**

1. Every child has the right:

   a. To life;

   b. To a name and nationality;

   c. To know and be cared for by his or her parents or legal guardians;

   d. Not to be subject to exploitative practices, neither to be required nor permitted to perform work which may be hazardous or harmful to his or her education, health or

ሐ) የመገንጠል ጥያቄ በሕዝብ ውሳኔው በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፤

መ) የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፤

ሠ) በሕግ በሚወሰነው መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡

5 በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፤ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው፡፡

6 የማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፤ ሕዝብ የራሱን ክልል የመመሥረት መብት ሥራ ላይ የሚውለው፤

ሀ) የክልል መመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፤

ለ) ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዘበ-ውሳኔ ሲያደራጅ፤

ሐ) ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፤ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፤

መ) የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፤

ሠ) በሕዝበ ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ

well-being;

e. To be free of corporal punishment or cruel and inhumane treatment in schools and other institutions responsible for the care of children.

2. In all actions concerning children undertaken by public and private welfare institutions, courts of law, administrative authorities or legislative bodies, the primary consideration shall be the best interest of the child.

3) Juvenile offenders admitted to corrective or rehabilitative institutions, and juveniles who become wards of the State or who are placed in public or private orphanages, shall be kept separately from adults.

4) Children born out of wedlock shall have the same rights as children born of wedlock.

5) The State shall accord special protection to orphans and shall encourage the establishment of institutions which ensure and promote their adoption and advance their welfare, and education.

**Article 37**

**Right of Access to Justice**

1. Everyone has the right to bring a justiciable matter to, and to obtain a decision or judgment by, a court of law or any other competent body with judicial

ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው፡፡

7 በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ «የክልሉ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ›› ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡

**አንቀጽ ፵**

**የንብረት መብት**

1 ማንኛውም በክልሉ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል፡፡

2 ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው፡፡

3 የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት

power.

2. The decision or judgment referred to under sub-Article 1 of this Article may also be sought by:

a. Any association representing the Collective or individual interest of its members; or

b. Any group or person who is a member of, or represents a group with similar interests.

**Article 38**

**The Right to Vote and to be Elected**

1. Every Ethiopian national, without any discrimination based on colour, race, nation,nationality, sex, language, religion, political or other opinion or other status, has the following rights:

a. To take part in the conduct of public affairs, directly and through freely chosen representatives;

b. On the attainment of 18 years of age, to vote and 21 years of age. To be elected in accordance with law;

c. To vote and to be elected at periodic elections to

መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው፡፡

4 የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ ነው። አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል፡፡

5 የክልሉ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

6 የመሬት ባለቤትነት የሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

7 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል፡፡

8 የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ ፵1</u>**

**<u>የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች</u>**

1 ማንኛውም የክልሉ ነዋሪና በክልሉ ውስጥ ለመኖር

any office at any level of government; elections shall be by universal and equal suffrage and shall be held by secret ballot, guaranteeing the free expression of the will of the electors.

2. The right of everyone to be a member of his own will in a political organization, labour union, trade organization, or employers' or professional association shall be respected if he or she meets the special and general requirements stipulated by such organization.
3. Elections to positions of responsibility with any of the organizations referred to under sub-Article 2 of this Article shall be conducted in a free and democratic manner.
4. The provisions of sub-Articles 2 and 3 of this Article shall apply to civic organizations which significantly affect the public interest.

**Article 39**

**The Rights of Nations, Nationalities and Peoples of the South Ethiopia Region**

In accordance with the provisions of the Ethiopian Federal Democratic Republic constitution, the Nations, Nationalities and Peoples of the Regional State have unconditional right of self-determination, including to secession. Accordingly, Nations, Nationalities and people have the right to:-

የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡

2 ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡

3 የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

4 የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶች ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፡፡

5 የክልሉ መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡

6 የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለኢኮኖሚ ጥገኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ኘሮግራሞችን ያወጣል፤ ኘሮጀክቶችን ያካሄዳል፡፡

7 የክልሉ መንግሥት ለክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

8 በክልሉ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው። መንግሥት የኢኮኖሚ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት፡፡

1. Preserve its identity and have it respected, promote and preserve its hertage, artifact and history, and use and develop its own language and culture;

2. Administer its own affairs within its own defined territory and effectively, impartially, and justly participate in the activites of the Federal government;

3. Establish its own governmental organizations pertinent to its geographical settlement and get fair representation in the State and Federal administration.

4. The right to self-determination, including secession, of every Nation, Nationality and People in the South Ethiopia Regional State can be exercised:-

a. When a demand for secession has been approved by a two-thirds majority of the members of the Legislative Council of the concerned Nation, Nationality or People;

b. When the Federal Government has organized a referendum which must take place within three years from the time it received the concerned

9 የክልሉ መንግሥት የባሕልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋፅዖ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

**አንቀጽ ፵2**

**የሠራተኞች መብት**

1 የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች፡-

ሀ) የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሰረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

መ) ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2 ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት እረፍት የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት

council's decision for secession;

c. When the demand for secession is supported by majority vote in the referendum;

d. When the Federal Government transferred power to the council of the Nation, Nationality or People that demanded secession/who has voted to secede; and

e. When the division of assets is effected in accordance with the law.

5. Nations, Nationalities and Peoples within the States have the right to establish, at any time, their own State.

6. The right of any Nation, Nationality or People to form its own state is exercisable under the following procedures:

a. When the demand for statehood has been approved by a two-thirds majority of the members of the Council of the Nation, Nationality or People concerned, and the demand is presented in writing to the State Council;

b. When the Council that received the demand has organized a referendum within one year to be held in the Nation, Nationality or People that made the demand;

c. When the demand for statehood is supported by a

እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3 እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

**አንቀጽ ፵3**

**የልማት መብት**

1 የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2 የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊና ክልላዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

3 የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የዜጎችን እድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፵4**

**የአካባቢ ደህንነት መብት**

1 ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡

majority vote in the referendum;

d. When the State Council will have transferred its powers to the Nation,Nationality or People that made the demand; and

e. When the new State created by the referendum without any need for application, directly becomes a member of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

7. Nation, Nationality or People" for the purpose of this Constitution , is a group of people who have or share large measure of a common culture or similar customs, mutual intelligibility of language, belief in a common or related identities, a common psychological make-up, and who inhabit an identifiable, predominantly contiguous territory.

**Article 40**

**The Right to Property**

1. The right of every dweller of the state to own private property shall be respected. Unless prescribed otherwise by law on account of public interest, this right shall include the right to acquire, to use and, in a manner compatible with the rights of other citizens, to dispose of such property by sale

2 የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት ተመጣጣኝ ድጋፍ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

<u>ምዕራፍ አራት</u>

<u>የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል</u>

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>የክልሉ መንግሥት አደረጃጀት</u>

<u>አንቀጽ ፬5</u>

<u>የክልሉ መንግሥት መሥራች አባላት</u>

1 የክልሉ መንግሥት መሥራች አባላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ ዎላይታ ዞን

ለ/ ጋሞ ዞን

ሐ/ ጌዴኦ ዞን

መ/ ጎፋ ዞን

ሠ/ ደቡብ ኦሞ ዞን

ረ/ ኮንሶ ዞን

or bequest or to transfer it otherwise.

2. "Private property", for the purpose of this Article, shall mean any tangible or intangible product which has value and is produced by the labour, creativity, enterprise or capital of an individual citizen, associations which enjoy juridical personality under the law, or in appropriate circumstances, by communities specifically empowered by law to own property in common.

3. The right to ownership of rural and urban land, as well as of all natural resources, is exclusively vested in the State and in the people. Land is a common property of the Peoples of the Regional State and shall not be subject to sale or to other means of exchange.

4. The farmers of the State have right to obtain land without payment and the protection against eviction from their possession. The implementation of this provision shall be specified by law.

5. The nomads of the State have the right to get the land necessary for farming or grazing free of charge and not to be displaced from their own lands. The implementation shall be determined by law.

6. Without prejudice to the execlusive right of People to the ownership of land, the State shall ensure the right of private investors to the use of land on the basis of payment arrangements to be determined by

ሰ/ አማሮ ልዩ ወረዳ

ሸ/ ዲራሼ ልዩ ወረዳ

ቀ/ ቡርጂ ልዩ ወረዳ

በ/ ባስኬቶ ልዩ ወረዳ

ተ/ ኼሌ ልዩ ወረዳ

2 ሁሉም የክልሉ መንግሥት መሥራች አባላት እኩል እውቅና፣ መብትና ሥልጣን አላቸዉ፡፡

**<u>አንቀጽ ፵6</u>**

**<u>የክልሉ አስተዳደር እርከኖች</u>**

1 የክልሉ መንግሥት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀበሌ የተዋቀረ ነው፡፡

2 የዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵7 ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ እንደተጠበቁ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሕግ መሰረት የሚቋቋሙ የየራሳቸው የዞን ወይም የወረዳ አስተዳደር ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፵7</u>**

**<u>አዳዲስ አደረጃጀቶችን ስለመመስረት</u>**

1 በክልሉ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት የራሳቸውን የአደረጃጀት መዋቅር የማቋቋም መብት አላቸው፤

2 የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስ ክልል የመመስረት መብት ሥራ ላይ የሚዉለዉ በዚህ ሕገ

law. Particulars shall be determined by law.

7. Any Ethiopian shall have the full right to the immovable property he builds and to the permanent improvements he brings about on the land by his labour or capital. This right shall include the right to alienate, to bequeath, and, where the right of use expires, to remove his property, transfer his title, or claim compensation for it. Particulars shall be determined by law.
8. Without prejudice to the right to private property, the Regional State may expropriate private property for public purposes subject to payment in advance of compensation commensurate to the value of the property.

**Article 41**

**Economic, Social and Cultural Rights**

1. Any inhabitant of the state and any Ethiopian who wishes to live in the state has the right to engage freely in any economic activity and to pursue occupation of his choice for his livelihood.
2. Any dweller of the state has the right to choose his means of livelihood, occupation and profession.
3. All inhabitants of the State have the right to equal access to publicly funded social services.
4. The Regional State has an obligation to allocate an ever increasing budget to provide with to the public health, education and other social services.

መንግሥት በአንቀጽ ፴9 በተደነገገዉ አግባብ ይሆናል፡፡

3 በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት በክልል የመደራጀት ጥያቄ የቀረበለት የክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ በደረሰዉ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም ጠያቂው በተሰጠው ምላሽ ካልተስማማ የጠያቂዉ ሕዝብ ምክር ቤት ተገቢውን የሕግ አግባብ ተከትሎ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዉ፤

4 በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አዲስ ክልል የተመሰረተ እንደሆነ በነባሩ ክልል እና አዲስ በሚደራጀው ክልል የሚኖረው የጋራ ሀብት ወይም የንብረትና ዕዳ ክፍፍል የሀገሪቱን የንብረት ሕግ፣ የፋይናንስ ሕግ እና ሲተዳደሩበት የነበረውን የበጀት ቀመር አጠቃቀም የተከተለ ሆኖ ርትዕ፣ ፍትህ እና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸውን ሚዛናዊ መርሆዎችን የተከተለ ይሆናል፤

5 በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው ቢኖርም በነባሩ ክልል እና አዲስ በሚደራጀው ክልል መካከል የሚደረግ የተሻለ የሕግ ስምምነትን አያስቀርም፤

6 ከክልል በታች የሚነሱ የአደረጃጀት እና የአስተዳደር መዋቅር ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት የሕዝቦችን ፈቃድ መሰረት ባደረገ መልኩ የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የክልሉ መንግሥት አካላት እና የሥልጣን ክፍፍል**

5. The Regional State shall allocate, as far as economic condition permit, resources to provide rehabilitation and assistance to the physically and mentally disabled, the aged, and to children who are left without parents or guardian.

6. The Regional State shall pursue policies that aim at creating job opportunities for the unemployed and the economic dependents and shall accordingly undertake programmes and project that creat job opportunities.

7. The Regional State shall take the necessary steps to widen opportunities for the inhabitants of the state to find gainful employment.

8. Farmers and Nomades have the right to receive fair price for their products, that would lead to improvement in their conditions of life and to enable them to obtain an equitable share of the national wealth commensurate with their contribution. The Regional state shall be guided by this objective when formulating economic, social and development policies.

9. The Regional State has the responsibility to protect and preserve cultural and historical antiquities and to contribute to the promotion of the arts and sports.

**<u>አንቀጽ ፵8</u>**

**<u>የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት</u>**

1 የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አለው፡፡

2 የክልሉ የመንግሥት ሕግ አውጭ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለው ሕዝብ ነው፡፡

3 የክልሉ ከፍተኛ ሕግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው፡፡

4 የክልል የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፵9</u>**

**<u>የክልሉ መንግሥት የሥልጣን ክፍፍል መርህ</u>**

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብዝሃነትን ባማከለ መልኩ በእኩል እዉቅና፣ ተመጣጣኝና ፍትሃዊ ሥልጣን የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፶</u>**

**<u>የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ በውል ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ መንግሥት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማናቸውም

**Article 42**

**Rights of Labour**

1. Factory and service workers, farmers, farm labourers, other rural workers and government employees whose work compatibility allows for it and who are below a certain level of responsibility፡-

a. Have the right to form associations to improve their conditions of employment and economic well-being. This right includes the right to form trade unions and other associations to bargain collectively with employers or other organizations that affect their interests.

b. The categories of workers mentioned in paragraph (a) of this sub-Article have the right to express grievances, including the right to strike.

c. Government employees who enjoy the rights provided under paragraphs (a) and b) of this sub - Article shall be determined by law.

d. Women workers have the right to equal pay for equal work.

ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መንግሥቱ፡-

ሀ. የክልሉ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና እቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤

ለ. የክልሉን ሕገ-መንግሥትና ሌሎች ሕጐችን ያወጣል ያስፈጽማል፤

ሐ. የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

መ. ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማው ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥትንና ይህንን ሕገ-መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፤

ሠ. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የስልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይኖርበታል፤

ረ. የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሠላምና ጸጥታ ይጠብቃል፤

ሰ. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፷8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፷8 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ

2. Workers have the right to reasonable limitation of working hours, to rest, to leisure, to periodic leaves with pay, to remuneration for public holidays as well as a healthy and safe work environment.

3. Without prejudice to the rights recognized under sub - Article 1 of this Article, laws enacted for the implementation of such rights shall establish procedures for the formation of trade unions and for the regulation of the collective bargaining process.

**Article 43**

**The Right to Development**

1. The inhabitants of the State have the right to improved living standards and to sustainable development.
2. The inhabitants of the State have the right to participate in national development activities. Particularly, to be consulted on the policies and projects affecting the community in which they are members.
3. The main objectives of the development activities

በሕግ መሰረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል፤

ሸ. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የራሱን በጀት ያወጣል፣ ያስፈፅማል፤

ቀ. የክልል መስተዳድሩና የግል ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

በ. የገጠር መሬት መጠየቂያ ክፍያን ይወስናል፣ ይሰበስባል፡፡

ተ. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

ቸ. በክልሉ ውስጥ በግል ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ በባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፤

ኀ. በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብርና የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን ይጠላል፣ ይሰበስባል፤

ነ. በክልሉ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

ኘ. በክልሉ ውስጥ በውሃ ላይ በሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

አ. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፺8 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን ይጥላል፣

of the State shall be to enhance the capacity of the Region's inhabitants for development and to meet their basic needs.

## Article 44

## Environmental Rights

1. The inhabitants of the State have the right to a clean and healthy environment.
2. All persons who have been displaced or whose livelihoods have been adversely affected as a result of the Regional State programmes shall have the right to commensurate monetary or alternative means of compensation, including relocation with appropriate State assistance.

# CHAPTER FOUR

# STRUCTURE OF THE REGIONAL STATE AND DIVISION OF POWER

## PART ONE

## STRUCTURE OF THE REGIONAL STATE

## Article 45

## Founding Members of the Regional State

1. The founding members of the Regional State are as

ይሰበስባል፤

ከ. ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር፡-

ሀ. በጋራ ከሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሠራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን በሕጉ መሰረት ይካፈላል፤

ለ. ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክሶችን በሕጉ መሰረት ይካፈላል፤

ሐ. ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕጉ መሰረት ይካፈላል፡፡

ኸ. በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል፣

ወ. ከደን የሚገኘውን የሮያልቲ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣

ዐ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

3 የክልሉ መንግሥት በዚህ አንቀጽ ከተቀመጠው ሥልጣንና ተግባር ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ለበታች የአስተዳደር እርከኖች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

follows.

A/ Wolaita Zone

B/ Gamo Zone

C/ Gedeo Zone

D/ Gofa Zone

E/ South Omo Zone

F/ Konso Zone

G/ Amaro Special Woreda

H/ Dirashe Special Woreda

I/ Burji Special Woreda

J / Basketo Special Woreda

K/ Allie Special Woreda

2. All the founding members of the Regional State shall have equal recognition, rights and powers.

## Article 46

## Administrative Hierarchies of the Regional State

1. The Regional State is organized with Regional, Zonal, Woreda, City administration, and kebele levels governans.
2. Consistent with the provision of sub-Article 6 of

ምዕራፍ አምስት

የክልሉ መንግሥት ምክር ቤቶች

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ ፶1

የክልሉ መንግሥት ምክር ቤቶች

የክልሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም የክልሉ ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት ናቸው፡፡

አንቀጽ ፶2

የምክር ቤቶች የወል ድንጋጌዎች

1 የክልሉ ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት የየራሳቸዉን የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስብሰባ ከማድረጋቸዉ አስቀድመዉ ዓመታዊ የጋራ መክፈቻ ስብሰባቸውን በአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ወር ላይ ያደርጋሉ፡፡

2 እያንዳንዱ ምክር ቤት፡-

ሀ/ የራሱን አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ ድምፅ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰይማል፡፡ ለሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፡፡

Article 47 of this Constitution the Nations, Nationalities and Peoples in the Region shall have their own zonal or woreda administration in accordance with law.The particulars shall be determined by law.

**Article 47**

**Forming New Structures**

1. The Nations, Nationalities and Peoples in the Region shall have the right to establish their own organizational structure according to this constitution;
2. The right of the Nations, Nationalities and Peoples of the Region to form its own state is exercisable in accordance with the provisions of Article 39 of this Constitution.
3. In accordance with the provisions of sub-Article 2 of this Article, if the State Council has not organized the referendum within one year of receiving the request, or if the requester does not agree with the response, the demanding council shall have the right to appeal to the House of Federation.
4. If a new Region is established in accordance with sub-Article 3 of this Article, the distribution of common wealth or property and debt in the existing Region and the newly organized Region shall follow the Country's property law, financial law, and the budget formula used in the administration,

ለ/ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

3 የእያንዳንዱ የምክር ቤት አባል፡-

ሀ/ በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡

ለ/ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

ሐ/ የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሰረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) ላይ የተደነገገው እንደአግባብነቱ በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት አለው፡፡

ሠ/ አንድ ሰዉ በአንድ ጊዜ የክልሉ ምክር ቤት እና የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም፡፡

**ክፍል ሁለት**

and shall follow the principles of equity, justice and other accepted principles of balance ;

5. Notwithstanding the provisions of sub-Article 4 of this Article, it does not preclude a better legal agreement between the existing Region and the newly organized Region;

6. The request to form administrative structure below the Regional hierarchy shall be answered based on the consent of the people concerned upon the law enacted by the State Council.

## PART TWO

## Regional State Bodies and Division of Powers

### Article 48

### Regional State Bodies

1. The state government has legislative, executive and judicial powers.
2. The State Councile is the legislative body of the State; it is the highest authority of the Regional

**ስለክልሉ ምክር ቤት**

**አንቀጽ ፶3**

**ስለክልሉ ምክር ቤት አባላት**

1 የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በምስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡

2 የምክር ቤት አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡ የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ የክልሉ ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ መሰረት ይወሰናል፡፡

3 የክልሉ ምክር ቤት አባላት የመላው የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ ተገዥነታቸውም ፡-

ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ፣

ለ/ ለሕዝብ እና

ሐ/ ለሕሊናቸው ብቻ ይሆናል፡፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ያሉ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በየደረጃው ለሚገኙ የምክር ቤት አባላት ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

**አንቀጽ ፶4**

**የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

1 የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት የክልሉ

State and is accountable to the people whom it represents.

3. The Executive Councile is the highest State organ and is accountable to the State Council.

4. The State's judicale power shall execusively be vested in the Region's Courts.

**Article 49**

**The Principle of Division of Powers of the Regional State**

The nations, nationalities and peoples in the region have the right to equal recognition, proportional and fair power distrubition in concederation of the diversity. The particulars shall be determined by law.

**Article 50**

**Powers and Functions of the Regional State**

1. All powers and functions except those dully and explicitly reserved to the Federal State or otherwise to the Federal and Regional States in common within the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall henceforth be the powers and functions of the Regional State

ከፍተኛ የሕግ አውጪ አካል ነው፡፡

2 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነው፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

ሀ) በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት የፌዴራሉን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል፡፡

ለ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵7 ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ዉስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደር አካባቢዎችን በሕግ መሰረት ያቋቁማል፡፡

ሐ/) የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሉ ከሌሎች ክልል መንግስታት ጋር የሚደረገውን ስምምነት መርምሮ ያጸድቃል፤

መ/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድር ይመርጣል፡፡ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያጸድቃል፤

ሠ) የዋና ኦዲተርና የቁጥጥር አካሉን ያቋቁማል፤

ረ/ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤ የጸጥታና የፖሊስ ኃይሉን ያቋቁማል፤

2. Without prejudice to the provisions stipulated under sub-art. 1 of this Article , the Regional State:-

a. Sets out the economic and social development policy, strategy and plan of the regional state and works towards their implementation thereof;

b. Enacts and executes the constitution and other laws of the regional state;

c. Administers land and natural resources, in accordance with laws enacted by the federal state;

d. Constitutes a regional government on the basis and objective of self administration, establishes and builds up a democratic order, wherein the rule of law prevails, safeguards and defends the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as well as this constitution;

e. Enacts laws regarding working conditions of civil servants of the regional government and strives towards their implementation thereof, provided, however, that it shall take into account the standard criteria of the country in relation to education, training and working experience, while executing such laws;

f. Organizes and directs the regional police force and thereby protects peace and

| | |
|---|---|
| ሰ/ የክልሉን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲና ፕሮግራሞችን ያጸድቃል፤ | security of the regional state; |
| ሸ/ የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፡፡ ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፡፡ የክልሉን መንግሥት በጀት ያጸድቃል፡፡ | g. Without prejudice to the provisions of art. 28 sub-arts 1 of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Art. 28 of this constitution, grants amnesty or pardon in accordance with law; |
| ቀ/ ለማኅበራዊ አገልግሎት መስፋፋትና ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፡፡ | h. Levies and collects taxes and other duties on any source of revenue reserved to the jurisdiction of the regional state as well as prepares and issues its own budget na implements thereof; |
| በ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት እና ምክትል ፕሬዚደንት እና የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር ሹመት በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት ያጸድቃል፤ | i. Levies and collects income tax on and from the employees of the regional government and private enterprizes; |
| ተ/ የዳኞችን ሹመት በዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት ያጸድቃል፤ | j. Determines and collects rural land userfees; |
| | |
| ቸ/ የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤ | k. Levies and collects agricultural income tax; |
| ኀ/ ለክልሉ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፣ | |
| ነ/ የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል፤ | l. Levies and collects tax on and from the revenue generated from houses and properties under private ownership situated in the regional state, and collects rental payments from houses and other forms of property under public ownership of the regional government; |
| ኘ/ በሕግ መሰረት ምህረት ያደርጋል፤ | m. Levies and collects business profit, personal income, sales and excise taxes on and from development enterprizes operated under the ownership of the regional government; |
| አ/ የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ | |

ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ ፶5**

**የፖለቲካ ሥልጣን**

1 በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ያደራጃል ወይም ያደራጃሉ፣ ይመራል ወይም ይመራሉ፤

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በየደረጃዉ ለሚገኙ አስተዳደር ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ ፶6**

**የአፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

አፈጉባዔው፤ -

1 የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፤

2 ምክር ቤቱን በመወከል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፡፡

3 ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነዉን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡

4 የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት በሕግ ይወስናል፡፡

5 የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል፡፡

6 በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፡፡

n. Levy and collect profit and sales taxes on individual traders carrying out a business within the state;

o. Levy and collect taxes on income from transport services rendered on waters within the state;

p. Consistant with the provisions of sub-Article 3 of Article 98 of the Federal Constitution, State shall levy and collect taxes on income drived from mining operations, and royalties and land rentals on such operations;

q. Together with the federal state:-

a) Shares, in accordance with law, business profit, personal income, sales and excise taxes generated from development enterprises jointly established thereto;

b) Shares, in accordance with law, sales and other taxes derived from business profits of companies and dividends due to share-holders;

c) Shares, in accordance with law, income tax derived from large-scale mining and all petroleum and gas

**አንቀጽ ፵7**

**የምክትል አፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

1 በአፈጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2 አፈጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

**አንቀጽ ፵8**

**የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜ እና የሥራ ዘመን**

1 ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው ከተገኘ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

2 የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ለአምስት ዓመታት ነው፡፡ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡

3 ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፤

4 የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፤ ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈጻሚ አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉ ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፵9**

operations and royalties on such operations.

r. Determines and collects, fees generated from licensing and delivery of other services rendered by the organs of the regional government;

s. Fixes and collects royalty to be derived from forest resources;

t. Where natural calamity is faced or any disease endangering public health declares and implements state of emergency decree throughout the regional state.

3. The Regional State where it deems necessary, may delegate its power and functions to the next administrative hierarchies.

**CHAPTER FIVE**

**THE COUNCILS**

**PART ONE**

**GENERAL**

**Article 51**

**The Councils**

**የክልሉ ምክር ቤት የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

1 በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ተገልጾ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው ላይ ከተገኙት የምክር ቤት አባላት ውስጥ በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡

2 ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሠራሩና የሕግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ፷**

**ስለክልሉ ምክር ቤት መበተን**

1 ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤቱ የሥልጣን ዘመን ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል፡፡

2 በጣምራ የክልሉን መንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተበትኖ በምክር ቤቱ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት ርዕሰ መስተዳድሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመመስረት ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ የክልሉ ምክር ቤት ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የክልሉ ምክር ቤት የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡

4 ምርጫው በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ የክልል ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡

There shall be two Councils; the State Council and the Council of Nationalities.

**Article 52**

**Common Provisions of the Councils**

1. The State Council and the Council of Nationalities shall held joint session in the first month of the New Year before holding their respective annual session of the fiscal years.

2. Each Council shall:

A/ Appoints his own Speaker and Deputy Speaker in the Council on behalf of the political organization or political organizations that has the majority of votes. As required, establishes permanent and ad hoc committees.

B/ The term of office shall be one election term. The council shall meet at least twice a year.

3. Members of each council :

A/ No member of the Councils may be prosecuted on account of any vote he casts, or opinion he expresses in the council, or shall any administrative action be taken against any member on such

5 የክልሉ ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ክልሉን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሄድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችንና ድንጋጌዎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም፡፡

6 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በቀበሌ ምክር ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የብሔረሰቦች ምክር ቤት</u>**

**<u>አንቀጽ ፷1</u>**

**<u>የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት</u>**

1 የብሔረሰቦች ምክር ቤት በክልሉ የሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቢያንስ በሁለት አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነዉ፡፡

2 እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በአንድ ሚሊዮን አንድ ተጨማሪ አባል ይወከላል፡፡

3 የብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት ከፌዴራል ሕዝብ ተወካዮች እና ክልል ምክር ቤት ተመራጭ ውጭ በየደረጃዉ ከሚገኙ ምክር ቤት ወይም በአስተዳደር ምክር ቤት ከየብሔረሰቡ የሚወከሉ አባላት ይሆናሉ፡፡ ውክልናቸው በሚመለከተው የዞን ወይም ወረዳ ምክር ቤት የጸደቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

ground;

B/ No member of the Councils may be arrested or prosecuted without the permission of the concerned Council except in the case of flagrante delicto;

C/ May, in accordance with law, lose his mandate of representation upon lose of confidence by the electorate;

D/ Sub article 3(c) of this article shall accordingly be applicable to councils of lower hierarchies;

E/ No one may be a member of the State Council and Council of Nationalities simultaneously.

**PART TWO**

**STATE COUNCIL**

**Article 53**

**Members of the State Council**

1. Members of the State council shall be: Elected for a term of five years by free, direct and fair election conducted through secret ballot.

**<u>አንቀጽ ፷2</u>**

**<u>የብሔረሰቦች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

**ምክር ቤቱ፤ -**

1 የክልሉን ሕገ መንግሥት የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2 የክልሉን የበጀት ቀመር ይወስናል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

3 ፍትሐዊ የሆነ የልማት ተጠቃሚነት፣ የሥልጣንና የሀብት ክፍፍል እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ስምሪት ሚዛናዊነትን ያረጋግጣል፣ በሚመለከተው አካል ተገቢ እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

4 የክልሉን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ያደራጃል፤

5 የክልሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፤ ሕዝቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲጠናከርና እንዲጎለብት ያደርጋል፤

6 በክልሉ ውስጥ በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች እንዲሁም በብሔሮች ብሔርሰቦች እና ሕዝቦች መካከል በሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ይፈልጋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

7 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የዞንና የወረዳ አስተዳደር መብት በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሰረት ይወስናል፡፡

8 በክልሉ ምክር ቤት ልዩ ውክልና የሚያስፈልጋቸዉ ማኅበረሰብ ክፍሎችን በሕግ መሰረት ይወስናል፡፡

9 የብሔረሰቦች ታሪክ፣ ባሕል፣ ቋንቋ የሚጠናበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

2. Elected from among candidates in each electoral district by a plurality of votes casted. The minority Nationalities and Peoples shall have seats in the State Council, on the basis of special representation. Particulars shall be determined by law.

3. They are representatitve of the peoples of the State as a whole, and they are accountable to:

A/ The constitution,

B/ The Public; and

C/ Their own conscience.

4. The provisions of this Article sub-Article 1 to 3 are heirarchically applicable to lower Councils.

**Article 54**

**Powers and Functions of the State Council**

1. The state council is the highest legislative body of the state according to this constitution.
2. Without prejudice to the provisions of the Federal Constitution, the highest political authority regarding the internal affairs of the state is vested in

0. የክልሉ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ በማመንጨትና በማሻሻል ሂደት ዉስጥ ይሳተፋል፤

01 ከአጎራባች ክልል መንግስታት ጋር በሚነሱ አለመግባባቶችና የወሰን መካለል ጥያቄዎችን አጥንቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

02 የራሱን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤

03 የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ፷3

## የብሔረሰቦች ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ፣ የሥራ ዘመን እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1 ከምክር ቤቱ አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኘ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡ ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈዉ ስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ድምፅ ሲደገፍ ብቻ ነዉ፡፡

2 የምክር ቤቱ አባላት ድምፅ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነዉ፡፡

3 ምክር ቤቱ ስለዉስጣዊ አሠራሩ፣ የስብሰባ አመራር ሥነ-ሥርዓት እና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

4 ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

5 የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አንድ የምርጫ ዘመን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ፷4

## የብሔረሰቦች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

the State Council.

3. Consistent with the provisions of sub- article 1 and 2 of this article, the State Council shall have the following powers and functions:

A/ Based on this constitution, issues different laws that are consistent with the Federal and other laws;

B/ Establishes additional administration hierarchies or self- administering regions, by taking into account the size of the population, the width and socio-economic activities within the region. Determines administrative structures as per article 47 sub-article 6 of this Constitution;

C) without prejudice to the powers vested to the Federal Government, it shall ratify agreements concluded by the Executive body;

D/ Elects Chief executive from among the members of the council. Approves the appointment of members of the Executive Council up on recommendation by Chief Executive;

E) Esatblishes the Auditor General and Control Office;

F/ Issues regulations necessary for the maintenance of peace and security of the region, and establish

1 የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፤

2 ምክር ቤቱን ይወክላል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፤

3 ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የወሰደውን የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል፤

4 የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፡፡

5 የምክር ቤቱን ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል፤

6 በምክር ቤቱና በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

**<u>አንቀጽ ፳5</u>**

**<u>የብሔረሰቦች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 አፈጉባዔው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

2 በአፈጉባዔው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

**<u>ምዕራፍ ስድስት</u>**

**<u>የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት</u>**

**<u>አንቀጽ ፳6</u>**

**<u>የክልሉ መንግሥት የአስፈጻሚነት ሥልጣን</u>**

1 የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነዉ፡፡

security and police force.

G/ Approves social and economic policies and programs of the state;

H/ Issues laws regarding the income sources of the State. Approves the State budget;

I/Establishes institutions necessary for the promotion of social services and economic development.

J/ Appoint the President and Vice-President of the State Supreme Court, the Auditor General and Vice - Auditor General;

K/ Approves the appointment of judges presented by Judicial Council;

L/ Issues laws regarding the State civil servants and their working conditions of services;

M/ Declare a state of emergency according to the authority given to the Regional State.

N/ Call and request the Chief Executive and other State Officials. Investigate the Executive's conduct

2 ርዕሰ መስተዳድሩ እና የመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ፡፡

3 የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸዉ በጋራ ለሚሰጡት ዉሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

4 "መስተዳድር" ማለት የክልሉ መንግሥት የሕግ አስፈጻሚው አካል ነው፡፡

**አንቀጽ ፷7**

**የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት**

1 የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነዉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

2 የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነዉ፡፡

3 የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነዉ፡፡

4 የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነዉ ዉሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፷8**

**የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

የፌዴራል ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1 በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራል መንግሥት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን

and discharege of its responsibilities.

O/ Grantes an amnesty persuant to the law.

P/Organizes its own office. Particulars shall be determined by law.

**Article 55**

**Political Power**

1. A political party or poletical parties with a majority of seats in the State Council shall form the Executive and lead it;

2. The provisions of this Article sub-Article 1 shall accordingly be applicable to each council heirarchically.

**Article 56**

**Powers and Functions of the Speaker**

He Shall:-

1. Call and presides the meetings of the council;
2. Direct all administrative affairs on behalf of the

ያረጋግጣል፤ መመሪያዎችን ያወጣል፤

2 በሕግ በሚወሰነው መሰረት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት፣ ሌሎች አስፈጻሚ አካላትና ልዩ ልዩ ተቋማትን ያደራጃል፤ ይቆጣጠራል፤ ይመራል፡፡

3 የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት በወሰነው የበጀት ቀመር መሰረት የክልሉን መንግሥት በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

4 የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ የሕግ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፤ የተወሰነውንም ያስፈፅማል፡፡

5 በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፡፡

6 የክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሰረት ደንቦችን ያወጣል፡፡

7 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው የጊዜ ወሰን ውስጥ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

8 በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ 3(ረ) መሰረት የሚቀርቡለትን ኃላፊዎች ይሾማል፡፡

9 የክልሉ ቅርሳ ቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

0. በክልሉ ምክር ቤትና በሕግ መሰረት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ ፭9**

**የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አሰያየምና የሥራ ዘመን**

1 ርዕሰ መስተዳደሩ በክልሉ ምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች

council.

3. Enforce all disciplinary actions, the State Council take on its members.
4. Determined by law, organize of the office of the State Council.
5. Coordinates standing and ad hoc committees of the council.
6. Perform other duties that may be entrusted to him by law.

**Article 57**

**Powers and Function of Deputy Speaker**

1. He shall perform duties which shall be specifically entrusted to him by the Speaker;
2. He acts on behalf of the Speaker in his absence or unable to exercise his powers and functions;

**Article 58**

**Session of the State Council, Duration of its term**

1. The presence of two-thirds of the members of State Council constitutes a quorum;
2. Members of the State Council are elected for five years. Election for the new State Council shall be concluded one month prior to the expiry of the Council's term. The new council shall convene within one month of the conclusion of the election.

አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል ይሰየማል፡፡

2 በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፶፱</u>**

**<u>የርዕሰ መስተዳደሩ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

1 ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድር ሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ እና የክልሉ ፕሬዚደንት ነው፡፡

2 በዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፡-

ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፣

ለ/ የክልሉ ምክር ቤትና መስተዳድር ምክር ቤት እንዲሁም የዞን ምክር ቤቶች በየበኩላቸው መክረው ያጸደቋቸውን አዋጆችና ደንቦች በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል፡፡ ርዕሰ መስተዳድሩ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይዉላል፤

ሐ) የክልሉ ምክር ቤት እና መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፡፡

መ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የክልሉን ዋና ኦዲተር እና ምክትል ዋና ኦዲተር ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ

3. The speaker may call an extraordinary meeting of the council. He is also obliged to call an extraordinary meeting of the council at request of more than one-thirds of the members;

4. Meetings of the Council shall be public, the Council may, however, hold a closed meeting at the request of the Executive Council or members' of the council by a decision of more than half of the members.

**Article 59**

**Decision Making Procedure of the State Council**

1. Unless otherwise specified in this constitution, all decisions of the Council shall be passed by the majority vote of the members present.

2. The Council shall adopt rules and procedures regarding the organization of its work and of its legislative process.

**Article 60**

| | |
|---|---|
| ያስጸድቃል፡፡ | **Dissolution of the State Council** |
| ሠ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር እና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላትን ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ሹሜታቸውን ያስጸድቃል፡፡ | 1. With the consent of the Council, Chief executive may cause the dissolution of the council before the expiry of its term in order to hold a new election; |
| ረ/ የክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማትና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) እና (ሠ) ስር ከተዘረዘሩት ውጪ የሆኑ የክልል አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችን እና ምክትል ኃላፊዎችን ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያስጸድቃል፡፡ | 2. The chief executive, may, invite political parties to form a coalition government within two weeks, if the Executive Council of a previous coaltion is dissolved because of the loss of its majority in the Council. The state council shall be dissolved and new elections shall be held if the political parties can not agree to the continuation of the previous coaltion or to form a new majority coalition. |
| ሰ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዛዊነት መድቦ ያሰራል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በጊዜያዊነት የሚመደቡት ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች መካከል ይሆናል፡፡ | 3. If the Council is dissolved pursuant to sub article (1) or (2) of this article, new election shall be held within six months of its dissolution. |
| ሸ/ የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅና ሕግንና ሥርዓት ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ | 4. Within fifteen days of the completion of the election, the new Council shall convene. |
| ቀ/ በክልሉ የሚገኙትን የበታች የመስተዳድር እርከኖችን ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ | 5. Following the dissolution of the Council, the previous ruling party or parties shall continue as a caretaker government. Beyond conducting the day to day affairs of government and organizing new election, it may not enact proclamation, regulations or decrees, nor may it repeal or amend any existing law. |
| በ/ የክልሉን ምክር ቤት እና የክልሉን ብሔረሰቦች ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፡፡ | |
| 3 የክልሉ ምክር ቤትና የብሔረሰቦች ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ይከፍታል፣ | |

4 በሕግ የተሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ ፸1**

**የምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ርዕሰ መስተዳድር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሾም ሆኖ፡-

1 ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፤

2 በርዕሰ መስተዳድሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

3 ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

**አንቀጽ ፸2**

**የርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት**

1 ርዕሰ መስተዳደሩ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

2 የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል፤

3 የጽሕፈት ቤቱ አወቃቀር፤ አደረጃጀት፤ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ ፸3**

**ስለ ኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊ እና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም**

የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና አስተዳደራዊ ሥራዎችን የሚያከናዉኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች፣

6. The provisions of this article shall accordingly be applicable to zonal, woreda, city administration and kebele councils.

**PART THREE**

**COUNCIL OF NATIONALITIES**

**Article 61**

**Members of the National Council**

1. The Council of Nationalities is composed of representatives of Nations, Nationalities and Peoples at least by two members.
2. Each Nation, Nationality or People shall be represented by one additional representative for each one million of its population.
3. The members of the Council of Nationalities shall be the members of each Nation represented by the councils at each level or the administrative council, except for the elected representatives of the Federal House of Peoples' and the State council. Their representation shall be approved by the relevant Zone or Woreda council.

**Article 62**

**Powers and Functions of the Council of Nationalities**

ኮሚሽኖች፣ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች፣ ኢንስቲትዩቶች፣ የአስተዳደር እና የልማት እንዲሁም ሌሎች ተቋማት እንደ አስፈላጊነታቸዉ በሕግ ይቋቋማሉ፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ ፸4

### ስለ ነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1 በክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቋሟል፡፡

2 የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፤

### አንቀጽ ፸5

### ስለ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካላት

የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴4 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ፡፡

### አንቀጽ ፸6

### የዳኝነት ሥልጣን

1 የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡

The Council Shall:

1. Interpret the State constitution;
2. Prepares, approves and determines the budget formula of the region. The particulars shall be determined by law.
3. Ensure the fair distribution of development, power, resource, and ensures the balance in public servant deployment in governmental offices. Makes an appropriate action is taken by the concerned body. The particulars shall be determined by law.
4. Organize the Council of Constitutional Inquiry ;
5. Strengthens and develops the unity of the nation, nationalities and peoples of the region based on equality and consent;
6. Finds solutions to disputes arising between administrative levels in the region as well as ethnic groups and peoples. The details are determined by law;
7. As per the constitution, decide over the questions regarding administration of zonal or woreda structures.
8. According to the law, shall decide the sections of society that need special representation in the council.
9. Create favorable condition in which history, culture and language of the Nationalities be studied;

2 በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ አካል ተጽእኖ ነፃ ነው፡፡

3 ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፣ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡

4 ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜው ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፡-

ሀ/ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሰረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን፣ ወይም

ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን እና

ሐ/ የጉባዔው የመጨረሻ ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና ሲጸድቅ፡፡

5 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አንድ ዳኛ ከዳኝነት ሥራው የሚያስነሳ ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባዔው ከወሰነበት ጉዳዩ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ እስኪታይ ድረስ ከዳኝነት ሥራው ታግዶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

6 የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም፤

**<u>አንቀጽ ፸7</u>**

**<u>የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን</u>**

1 የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በወረዳ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል፡፡

10. Participates in the process of initiations and amendments of the State constitution;

11. Study, disputes between neighboring States and questions of terriotral delimitation, submit to the House of Federation and follow up the implementation.

12. Submits its own budget to the State Council for approval;

13. Organizes its own office. Particulars shall be determined by law.

**Article 63**

**Meeting, Term of Office and Decision-Making of the Council of Nationalities**

1. If two-thirds of the council members are present, it will be a plenary session. Any decision will be passed only when supported by more than half of the members of the council present at the meeting.
2. Council members can vote only when they are present in person.
3. The Council may enact code of conduct and meeting procedure for its members.
4. The Council shall hold regular meeting at least twice a year.
5. The term of office of the Council shall be one electoral term.

2 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡-

ሀ) ክልላዊ ጉዳዮች በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን፤

ለ) በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን እና

ሐ) ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት እና በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል በክልሉ ጉዳዮች ላይ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

መ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡

ሠ) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉን ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላትን እና ሠራተኞችን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድ በጀቱን ያስተዳድራል፡፡

3 የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈጽሙትን የፌዴራል የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን የገንዘብ ወጪዎች በተመለከተ ከፌዴራል መንግሥት ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል፡፡

4 የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ሀ) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከሚኖረው የዳኝነትሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ

**Article 64**

**Powers and Functions of the Speaker of the Council of Nationalities**

1. Convenes and presides over the regular and urgent meetings of the Council;
2. Represents the council, directs all administrative activities;
3. Enforce disciplinary action taken by the council against its members;
4. Organizes the office of the council, the details of which is determined by law.
5. Coordinates the ad hoc and permanent committees of the council;
6. Performs other duties assigned by the council and the law;

**Article 65**

**The Deputy Speaker of the National Council**

1. He acts on behalf of the Speaker in his absence or unable to carry out his powers and Functions;
2. Performs the tasks assigned by the Speaker;

**CHAPTER SIX**

ፍርድ ቤት የዳኝነትሥልጣን አለው፤

ለ) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡

ሐ) የክልሉን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤቱን እና በሥሩ ያሉትን የወረዳና የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶችንና ሠራተኞችን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለዞን ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳዲራል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

5 የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በክልሉ የበታችኛውና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው፡፡.

6 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 4 እና 5 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ የከፍተኛ እና የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ተግባርና ሥልጣን ዝርዝር በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ፷8

## የዳኞች አሿሿም

1 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፐሬዚደንትና ምክትል ፐሬዚደንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፤

2 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፐሬዚደንትና ምክትል ፐሬዚደንት እና የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች

## EXECUTIVE COUNCIL

## Article 66

## Power of the Executive Council

1. The highest executive power of the State is vested in the Chief Executive and the Executive Council.
2. The Chief Executive and the Executive Council are accountable to the State Council.
3. In the exercise of State functions, members of the Executive Council are collectively responsible for all the decisions they make as a body.
4. "Government" means the executive body of the State.

## Article 67

## The Executive Council

1. The Executive Council is composed of the Chief Executive, Deputy Chief Executive and the memebers of Heads of Bureaus. Particulars shall be determined by law.
2. The Chief Executive shall be the Chairman of the Executive Council.
3. The Executive Council is accountable to the Chief Executive.

ፕሬዚደንት በዞን አስተዳዳሪ አቅራቢነት በዞን ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

3 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

4 የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞችን ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት እጩ ዳኞች እንዲሁም የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት በከፍተኛ እና በወረዳ ፍርድ ቤቶች እጩ ዳኞች ላይ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞችን ሹመት ያጸድቃል፡፡

5 በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች የዲስፕሊንና የዝውውር ጉዳይ በዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ይወሰናል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

6 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከፈቃዱ ውጭ ከኃላፊነቱ የሚነሳው፡-

ሀ/ በከባድ ወንጀል የሚያስጠይቅ ተግባር መፈጸሙ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ጉልህ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ካጣ፣

ሐ/ በሕመም ምክንያት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት

4. The Executive Council is accountable to the State Council for the decision it makes.

**Article 68**

**Powers and Functions of the Executive Council**

In accordance with the provisions of the Federal Constitution, the Executive Council shall have the following powers and functions:-

1. Insures the implementation of laws and decisions issued by the State Council and the Federal Government. It shall issue directives;
2. Organize, control and direct the Executive Council, Executive Bodies and various institutions of the State.
3. The regional government, according to the budget formula approved by the Council of Nationalities, prepares a budget and presents it to the State Council, and implements it when it is approved.
4. Formulates economic and social policies and strategies of the State, submit draft laws to the State Council, when approved, it shall implement it.
5. Ensures the observance of law and order in the State.
6. Issues regulations pursuant to powers vested in it by the State Council.

መወጣት ካልቻለ፣እና

መ/ በፊደል (ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) በተጠቀሱት ምክንያቶች መነሻ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአብላጫ ድምፅ ሲፀድቅ ነው፡፡

7 ከኃላፊነቱ የተነሳ ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚደንት ከዳኝነት ሥራው የሚያስወጣ ጥፋት መፈፀሙ ወይም በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አለመቻሉ በጉባዔው ተረጋግጦ በክልሉ ምክር ቤት እንዲሰናበት ካልተወሰነ በስተቀር በዳኝነት ሥራው ሊቀጥል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፷9

## ስለ ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም

1 በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት፣ የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፤

2 የጉባዔው አደረጃጀት፣ የአባላት ዝርዝርና ስብጥር እንዲሁም ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር ሕግ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## ሕገ መንግሥት መተርጎም፣ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ መቋቋም እና ሥልጣንና ተግባር

## አንቀጽ ፸

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አወቃቀር

1 የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ

7. Declares a state of emergency. Within the time limit set by this constitution, submits it to the State Council for approval.

8. Appoints officials, in accordance with the power entrusted to it under Article 72 Sub-Article 3(f) of this Constitution.

9. It ensures that the heritage and natural resources of the region are given the necessary care and protection.

10. Performs other duties that may be entrusted to it by the State Council and by law.

## Article 69

## Appointment of the Chief Executive and Term of Mandate

1. The Chief Executive shall be elected, upon recommendation by a political party, or political parties that have the greatest number of seats in the State Council.

2. Unless otherwise provided in this constitution, the term of office of the Chief Executive is for the duration of the mandate of the State Councile.

## Article 70

## Powers and Functions of the Chief Executive

1. He is the Head, Chairman of the Executive Council

መንግሥት ተቋቁሟል፡፡

2 የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉ ናቸው፡-

ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት-- ሰብሳቢ፣

ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት-- ምክትል ሰብሳቢ፣

ሐ/ በርዕሰ መስተዳደሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፣

መ/ በአፈ-ጉባዔው አቅራቢነት ከክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ ሦስት አባላት ናቸው፡፡

3 የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሥራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ፹1

## ሕገ መንግሥቱን ስለ መተርጎም

1 በክልሉ ውስጥ የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡

2 የክልሉ ብሔረሰቦች ምክር ቤት የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

and President of the State.

2. Consistent with the provision of Sub- Article 1 of this Article, he shall have the following powers and functions:

A/ Lead, coordinate and represent the Executive Council;

B/ Signs laws submitted from State Council, Executive Council and Zonal Councils within fifteen days, Published in Debub Ethiopia Negarit Gazeta. If he does not sign it within fifteen days, It shall take effect without his signature;

C) Monitors the implementation policies, rules, guidelines and decisions issued by the State Council and Executive Council.

D/ Select nominees for the post of the President and Vice-President of the State Supreme Court, and the Auditor General and Vice- Auditor General and submit to the State Council for approval;

E/ Submitt to the State Council, for approval, nominees of deputy Chief Executive and Executive Council members.

**አንቀጽ ፹2**

**የአጣሪ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር**

1 የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ከክልሉ የሚመነጩ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን አለው፡፡ በሚደረገው ማጣራት መሰረት የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሀሳብ አዘጋጅቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

2 አጣሪ ጉባዔው በክልሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማንኛውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካይነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ ለመጨረሻ ውሳኔ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

3 በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባዔው፡-

ሀ/ የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል፡፡ ሆኖም በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ/ የሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕግ መንግሥታዊ ትርጉም አሰናድቶ ለብሔረሰቦች ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡

4 የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለብሔረሰቦች ምክር

F/ The economic, social and administrative institutions of the region and the heads and deputy heads of the regional executive offices other than those listed under sub-paragraph 2 (d) and (e) of this article shall be submitted to the regional government council and appointed.

G/ Subject to the provisions of sub-Article 2 (d) of this Article, when the State council is unable to convene, it shall temporarily assign the above-mentioned officials; the President and Vice President of the Supreme Court shall be assiagned provisionally from among the judges of the Supreme Court.

H/ Direct, and control the state's security police forces that maintain law and order in the State;

I/ Directs, coordinates and control administrative hierarchies;

J/ Shall call and convene a founding assembly of State Council and Council of Nationalities.

3. Shall open the joint annual session of the State Council and the Council of Nationalities ;
4. Discharge other responsibilities entrusted to him by law.

ቤት ያቀርባል፤ በሚመለከተው አካል ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**ምዕራፍ ዘጠኝ**

**የዞን፣ የወረዳ እና የቀበሌ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር**

**ክፍል አንድ**

**የዞን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር**

**አንቀጽ ፹3**

**የዞን አደረጃጀት**

1 ዞን ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፤

2 እያንዳንዱ ዞን የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የዞን ምክር ቤት፣

ለ/ የዞን አስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ/ የዳኝነት አካል ፡፡

**አንቀጽ ፹4**

**የዞን ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

1 የዞን ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት የተመረጡትን አባላት ጨምሮ ከየወረዳውና ከከተማ አስተዳደር ለዞን ምክር ቤት የሚመረጡ አባላት ያሉበት ሆኖ ይቋቋማል፡፡

2 በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች በዚህ ሕገ መንግሥት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤትና ለብሔረሰቦች ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣንና

**Article 71**

**Powers and Functions of the Deputy Chief Executive**

The Deputy Chief Executive shall be appointed by the State Council on the proposal of the Chief Executive and;

1. He is accountable to the Chief Executive and the Execuitve Council;
2. Performs the tasks assigned by the Chief Executive;
3. Substitute when the Chief Executive is absent or unable to perform his duties

**Article 72**

**Office of the Chief Executive**

1. The Chief Executive shall have his own office.
2. The office of the Chief Executive also serves as the office of the Executive Council;
3. The organization, structur, powers and functions of the office shall be determined by law.

**Article 73**

**Establishment of Economic, Social and Administrative**

ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን ምክር ቤቶች በዞኑ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡

3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የዞን ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የዞኑን የሥራ ቋንቋ ይወስናል፣

ለ/ በዞኑ ያለው ብሔረሰብ በቋንቋው ለመናገር፣ ለመጻፍ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ እንዲሁም ታሪኩን ለመንከባከብ ያላውን መብት ያስጠብቃል፣

ሐ/ በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራልና በክልል በወጡ ሕጎች ባልተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ እነዚህን ሕጎች በማይፃረር መልኩ ሕጎችን ያወጣል፡፡ የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ፈርሞ የላከውን ርዕሰ መስተዳድሩ በደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል፣

መ/ የክልል ምክር ቤት ያጸደቀውን ዕቅድ እና በጀት መሰረት በማድረግ የዞን ዕቅድና በጀት መርምሮ ያጸድቃል፣

ሠ/ ከዞን ምክር ቤት አባላት መካከል አፈጉባዔውን፣ ምክትል አፈጉባዔውን እና ዋና አስተዳዳሪውን መርጦ ይሰይማል፣

ረ/ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያጸድቃል፣

ሰ/ የከፍተኛ እና የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትነና ምክትል ፕሬዚዳንትን ከፍርድ ቤት ዳኞች ወይም ብቃት ካላቸው የሕግ ባለሙያዎች መካከል በዋና አስተዳዳሪዉ አቅራቢነት

**Institutions**

Various offices, commissions, institutes, administrations or development, and other organs that carry out and coordinate the economic, social and administrative activities of the Region may be established by law as necessary.

## CHAPTER SEVEN

## The Structure and Jurisdiction of the Courts

### Article 74

### Establishment of an Independent Judiciary

1. Independent Judiciary of the State is established by this Constitution;
2. Special or ad hoc courts which take judicial powers away from the regular courts or institutions legally empowered to exercise judicial functions and which do not follow legally prescribed procedures shall not be established.

### Article 75

### Customary and Religious Adjudication

Consistent with the provision of Sub-article 5 of Article 34 of this Constitution, the religious and traditional judicial bodies that were recognized and operated by

ይሰይማል፤

ሸ/ የዞን ዋና አስተዳዳሪን፣ ሌሎች ባለሥልጣናትንና የሥራ ኃላፊዎችን ለጥያቄ ይጠራል፤ አሠራራቸውን ይመረምራል፣

4 ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል፡፡

5 የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፡፡

**አንቀጽ ፹5**

**የዞን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔዎች**

1 የዞን ምክር ቤት በምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤት አባላት በሚመረጥ አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፤

2 በዚህ ሕገ መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር የተደነገገው ለዞን ምክር ቤት አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤

**አንቀጽ ፹6**

**የዞን ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ እና የሥራ ዘመን**

1 የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ

the government before the adoption of this Constitution shall be recognized and organized in accordance with this Constitution.

**Article 76**

**Judicial Power**

1. Judicial power in the State is exclusively vested in the Courts.
2. Courts of any level shall be free from intereference or influence of any governmental body, official, or any other source.
3. Judges shall exercise their functions in full independence. They shall be directed solely by the law.
4. No judge shall be removed from his duties before he reaches the legally determined retirement age except under the following conditions:

A/ When the Judicial Administration Council decides to remove him for violation of disciplinary rules or on grounds of gross incompetence or inefficiency; or

B/ When the Judicial Administration Council decides that a judge can no longer discharge his duty on account of illness; and

C/ When the State Council approve by a majority

ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡

2 የዞን ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያደርጋል፡፡

3 ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል፡፡

4 የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ ፹7

## የዞን አስተዳደር ምክር ቤት

1 የዞን ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የአስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተው ዞን ዋና አስተዳደር፣ ለዚሁ ዞን ምክር ቤት እና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡

2 የዞን አስተዳደር ምክር ቤት የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በዞኑ ውስጥ የሚገኙት የአስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ሆኖ ይቋቋሚል፡፡

3 የዞን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በጋራ ለወሰኑት ውሳኔና ለፈጸሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ፹8

## የዞን አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የዞን አስተዳዳር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር

vote the decisions of the Judicial Administration Council.

5. According to sub-paragraph 4 of this article, a judge should be suspended from his judicial work until the matter decided by the Judicial Administration Council approved by the State Council.
6. The retirement age of a judge may not be extended beyond the legally determined age.

## Article 77

## Jurisdiction and Structure of Courts

1. The judicial organ of the State comprises the State Supreme Court, High Court, and Woreda or First-Instance Court.
2. Supreme Court of the State:
   a) The highest and final judicial power over State matters;
   b) Exercise the jurisdiction of the Federal High Court;
   c) Has power of cassation over any final court decision on State matters which contains a basic error of law. Particulars shall be determined by law.

ይኖሩታል፡-

1 በክልሉ ምክር ቤት እና በፌዴራሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በዞኑ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤

2 የዞኑን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

3 የዞኑን ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፣ ለዞኑ ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲጸድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

4 ክልላዊ የሆኑ ፖሊሲዎችን ሳይቃረን የዞኑን ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ በዞኑ ምክር ቤት ያጸድቃል፤ የተወሰነውንም ያስፈፀማል፤

5 በዞኑ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤

6 ከክልሉ ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎች የማይፃረሩ መመሪያዎችን ያወጣል፤

7 የዞኑን ቅርሳ ቅርስና የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊው እንክብካቤና ጥበቃ የተደረገለት መሆኑን ያረጋግጣል፤

8 የዞን አስተዳደር ምክር ቤት በዳኞች ሹመት ላይ የበኩሉን አስተያየት ለዳኝነት አስተዳደር ጉባኤ ይሰጣል፡

9 ከዞን ምክር ቤትና ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡ ፡

**<u>አንቀጽ ፹9</u>**

**<u>የዞን ዋና አስተዳዳሪ አሰያየም እና የሥራ ዘመን</u>**

1 ዋና አስተዳዳሪው በዞን ምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤት አባላት በዞኑ ምክር ቤት በምርጫ ይሰየማል፤

2 በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር

d) Appeals against the decision of the Federal High Court of the State Supreme Court shall be heard by the Federal Supreme Court.

e) The Supreme Court shall draw up and submit directly to the State Council for approval of the administrative bnudget of the State courts. It shall implement the budget upon approval.

3. The Supreme Court of the State shall submit a request to the Federal Supreme Court for compensation from the Federal Government regarding the financial expenses incurred by the State Courts to perform the federal judicial functions on behalf of them.

4. The State High Court;

a) Has the jurisdiction of the Federal First Instance in addition to the State High Court jurisdiction;

b) The appeal from the decision of State High Court in its federal first instance juridcition shall be submitted to the State Supreme Court.

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን የዞኑ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፺</u>**

**<u>የዞን ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 ዋና አስተዳዳሪው የዞኑ አስተዳደር ሥራ መሪ፣ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና አስተዳዳሪ ነው፡፡

2 ዋና አስተዳዳሪው ለዞን ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተጠሪ ሆኖ፡-

ሀ/ የዞኑን አስተዳደር ምክር ቤት ይመራል፣ ይወክላል፣

ለ/ የፌዴራሉንና የክልሉን ሕገ መንግሥት፣ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በዞኑ ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ/ የዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያሾማል፡፡

መ/ የዞኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የወረዳ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችን ከፍርድ ቤቱ ዳኞች ወይም ብቃት ካላቸው የሕግ ባለሙያዎች መካከል መርጦ በምክር ቤት ያሰይማል፤ ለምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፤

ሠ/ የዞኑን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ሕግና ሥርዓት ለማስከበር የቆሙትን የጸጥታና የፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ረ/ በዞኑ የሚገኙትን የበታች አስተዳደር እርከኖችንና

c) The High Court shall draw up and submit directly to the Zonal Council for approval of the administrative budget of its own and woreda or first instance courts. It shall implement the budget upon approval. Particulars shall be determined by law.

5. Woreda or First Instance Court

Woreda or First Instance Courts are the lower and first level of courts in the region.

6. Subject to the provisions of Sub article 2, 4 and 5 of this article, the detail functions, powers and organization of the Supreme Court, High Court and the District or First Instance Courts shall be determined by law.

**Article 78**

**The Appointment of Judges**

1. The president and vice president of the State Supreme Court shall, upon recommendation by the Chief Executive, be appointed by the State Council.
2. The President and Vice President of the High Court and Woreda or First Instance Courts shall be appointed by the Zonal Council on the recommendation of the Zonal Administration.

| | |
|---|---|
| አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣<br><br>ሰ/ ለዞኑ ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በየጊዜው ሪፖርትያቀርባል፣<br><br>ሸ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፹9 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የዞኑን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፣<br><br>ቀ/ በዞኑ ምክር ቤትና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡ | 3. Judges of the Supreme Court, High Court, Woreda or First Instance Court of the State shall be appointed by the State Council on the recommendation of the Judicial Administration Assembly of the State. Particulars shall be determined by law.<br><br>4. The State Judicial Administration Council, before submitting nominees of the State's Supreme and High Court judges and Hign and Woreda Court judges to the State Council, has the responsibility to solicit and obtain the views of the Federal Judicial Administration Council and Zonal Adminstration Council respectively on the nominees and to forward those views along with its its recommendations. If the Federal Judicial Administration Council does not submit its view within three months, the State Council may approve the appointments. |
| **<u>አንቀጽ ፺1</u>**<br><br>**<u>የዞን ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>**<br><br>1 ምክትል ዋና አስተዳዳሪዉ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለዞኑ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፡-<br><br>ሀ) በዋና አስተዳዳሪውና በአስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤<br><br>ለ) ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡ | 5. Matters of code of professional conduct and discipline as well as transfer of judges of any court shall be determined by the State Judicial Administration Council.<br><br>6. The President or Vice President of the Supreme Court of the State can be removed from office without his permission:-<br><br>A/ When it is confirmed that an action involving a serious crime has been committed,<br><br>b/ If he loses significant work ability and |
| **<u>አንቀጽ ፺2</u>**<br><br>**<u>የዞን ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት</u>**<br><br>1 የዞኑ አስተዳደሪ ጽሕፈት ቤት በዋና አስተዳዳሪው ተመርጦ በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል፡፡<br><br>2 ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የተደነገገው ድንጋጌ ለዞን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት እንደ አግባብነቱ | |

ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የወረዳ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን**

**አንቀጽ ፺3**

**የወረዳ አስተዳደር አደረጃጀት**

1 የወረዳ አስተዳደር ከዞን አስተዳደር በታች የሚደራጅ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፤-

ሀ/ የወረዳ ምክር ቤት፣

ለ/ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት፣

ሐ/ የወረዳ የዳኝነት አካል፡፡

**አንቀጽ ፺4**

**የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር**

1 የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት አካባብ ውስጥ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ዕቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግሥት አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል፤

2 እያንዳንዱ የወረዳ አስተዳደር አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል መስተደደሩ የተደራጀበት ዞን

efficiency,

C/ If he is unable to fulfill his duties and responsibilities due to illness, and

D/ For the reasons mentioned in letters (a), (b) and (c) when the proposal is submitted to the State Council and approved by a majority vote.

7. If the president or vice president commits an offense that removes him from his judicial duties due to his responsibilities, or is unable to perform his duties properly due to illness, he may continue his judicial duties unless it is confirmed by the assembly and decided to be dismissed by the regional council.

**Article 79**

**Establishment of the State Judicial Judicial Council**

1. The State Judicial Council, where judges are represented by a majority vote, is hereby established;
2. The structure, compositions, powers and functions of the Council shall be determined by law.

**CHAPTER EIGHT**

**Interpreting the Constitution, Establishing Powers and Functions of the Constitutional Matters**

የበታች አካል ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፺5</u>**

**<u>የወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት</u>**

1 የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

2 የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፺6</u>**

**<u>የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግሥታዊ የሥልጣን አካል ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለመረጠው ሕዝብ ነው፡፡

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞችና የበጀት ረቂቅ መርምሮ ያጸድቃል፣

ለ. በወረዳ ውስጥ መሰረታዊ የግብርና ልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል፣

ሐ. ነዋሪው ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚነሳሳበትና የሚንቀሳንቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፣

**Article 80**

**Council of Constitutional Inquiry**

1. The Council of Constitutional Inquiry is established by this constitution;

2. The Council of Constitutional Inquiry shall have eleven members comprising ;

A/ President of the State Supreme Court, who shall serve as its president;

B/ The Vice President of the State Supreme Court, who shall serve as its vice president;

C/ Six legal experts, appointed by the State Council on recommendation by the Chief Executive, who shall have proven professional competence and high moral standing.

D/ Three members nominated by the Speaker from the members of the Council of Nationalities.

3. To ensure the efficiency, the Inquiry may extend its structures and working procedure. The particulars shall be determined by law.

መ. ከምክር ቤት አባላት መካከል አፈ-ጉባዔውን፣ ምክትል አፈ-ጉባዔውን እና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፣ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርብለትን የወረዳ አስተዳዳር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያጸድቃል፣

ሠ. የራሱን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣

ረ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ታክስን የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርን፤ የግብርና ውጤቶች ሽያጪ ግብርና ሌሎች የአገልግሎት ታክሶችንና ክፍያዎች መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፣

ሰ. ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ዉጭ ያለውን የወረዳውን የገቢ ምንጭ ይጠቁማል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወስናል፣

ሸ. የፌዴራሉና የክልሉ ሕግጋተ መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳውን ሠላምና ጸጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፤

ቀ. የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ፣ ሌሎች ባለሥልጣናትንና የሥራ መሪዎችን ለጥያቄ ይጠራል፣ አሠራራቸውንም ይመረምራል ፡ ፡

በ. የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፡ ፡

**<u>አንቀጽ ፺7</u>**

**<u>የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ</u>**

1 የወረዳ ምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ

**Article 81**

**Interpreting the Constitution**

1. When a constitutional dispute arises in the region, it will be decided by the Council of Nationalities.

2. The Council of Nationalities of the Region shall make a decision within thirty days on the constitutional issue presented to it by the Council of Constitutional Inquiry.

**Article 82**

**Powers and Functions of the Inquiry**

1. The Council of Constitutional Inquiry shall have powers to investigate constitutional dispute. Should the council, upon consideration of the matters, find it necessary to interpret the constitution, it shall submit its recommendation thereon to the Council of Nationalities.

2. When the claim to unconstitutionality of the laws issued by the state organs arises and is submitted to it by a court or a party to dispute, the Inquiry after examining the claim, shall submit its finding to Council of Nationalities for a final decision.

ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ተመርጦ በሚሰየም አፈ ጉባዔ እና ምክትል አፈ ጉባዔ ይመራል፡፡

2 በዚህ ሕገ መንግሥት ስለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባዔና ምክትል አፈ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር የተደነገገው ለወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ና ምክትል አፈ ጉባዔ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤

3 ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል፤

**አንቀጽ ፺8**

**የወረዳ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜ እና የሥራ ዘመን**

1 ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

2 ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሦስተኛው በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል፡፡

3 የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡

4 የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፡፡ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደርግበት ወቅት አፈጉባዔው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባዔው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

3. When issues of constitutional interpretation araise in the courts, the Council shall:

A/ When he does not find it necessary to interpret the constitution, immediately returns the case to the relevant court. However, any client aggrieved by the decision of the Council can appeal in writing to the Council of Nationationalities.

B/ If it believes that there is a need for constitutional interpretation, submit its decision to the Council of Nationalities for a final decision.

4. It may draft and submit rules and procedures, to guide its activities, implement up on approval of concerned body.

## CHAPTER NINE

## THE STRUCTURE, POWER AND FUNCTIONS OF THE ZONE, WOREDA, AND KEBELE

## PART ONE

## THE ZONE STRUCTURE, POWER AND FUNCTIONS

### Article 83

### The Zone Structure

1. The Zone is an administrative hierarchy next to

**አንቀጽ ፺9**

**የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት**

1 የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለወረዳው ምክር ቤት ነው፡፡

2 የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ እና የወረዳው አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡

**አንቀጽ ፻**

**የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

1 የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

ለ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የአስፈጻሚ አካላት ጽሕፈት ቤቶቻቸውን በበላይነት ያስተባብራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣

ሐ/ የወረዳውን የበጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

መ/ የወረዳውን ሰላምና ጸጥታ ይጠብቃል፣ የወረዳውን

Region.

2. Each Zone shall have the following components:

a/ The Zonal Council ,

b/ The Zonal Administrative Council ,

c/ The Judiciary.

**Article 84**

**Powers and Functions of the Zonal Council**

1. The Zonal Council shall be organized with the representatives elected to the Zonal Council from each Woreda and City administration, including those elected to the Regional Council;

2. Without prejudice to the powers and functions of the Houses of Peoples' Representative, House of Federation, the State Council and the Council of Nationalities, the Councils at the Zonal level shall exercise the highest political powers in the Zone.

3. Without prejudice to the provisions of sub-Article 2 of this Article, each zonal Council is accountable to the people who elected it, and shall have the following powers and functions:-

a/ Determine the working language of the Zone;

ጸጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፤

ሠ/ የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ዕቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል፣

ረ/ የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፣ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያነሳሳል፣

ሰ/ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም ቅርሳ ቅርስ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፤

ሸ/ በወረዳው ምክር ቤትና በዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2 የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸው ለሚፈጽሙት ተግባርና በጋራ ለሚያሳልፉት ውሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

**<u>አንቀጽ ፻1</u>**

**<u>የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አሰያየም እና የሥራ ዘመን</u>**

1 ዋና አስተዳዳሪው በወረዳው ምክር ቤት አብላጫ ድምፅ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤት አባላት በምርጫ ይሰየማል፤

2 በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳው ዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ ፻2</u>**

b/ Protect the rights of Nationalities to speak, write, develop their language and preserve their history, and monitor its implementation.

c/ Without prejudice to the powers vested in the State Council by this Constitution, it shall enact laws in a manner that does not contradict these laws on matters not covered by federal and state laws. Laws signed by the Speaker of the Zonal Council shall be submitted to the Chief Executive thereby published in Debub Ethiopia Negarit Gazeta.

d/ Examines and approves the Zonal plan and budget based on the plan and budget allocated and approved by the state Council .

e/ Select and appoint the Speaker, Deputy Speaker and Chief Administrator from among the members of the Zonal Council .

f/ Examine and approve the appointment of members of the Zonal Administrative Council submitted to it by the Chief Administrator .

g/ Appoint presidents and vice-presidents of the High and Woreda courts from among the Judges of the court or competent legal professional on the recommendation of the Chief Administrator.

h/ Call and examine the Chief Administrator of the

**<u>የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 ዋና አስተዳዳሪው የወረዳው አስተዳደር ሥራ መሪ፣ የአስተዳደሩ ምክር ቤት ሰብሳቢና የወረዳው አስተዳዳሪ ነው፡፡

2 ዋና አስተዳዳሪው ለወረዳ ምክር ቤትና ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪ ሆኖ፡-

ሀ/ የወረዳውን አስተዳደር ይወክላል፣

ለ/ የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት ይመራል፣

ሐ/ የፌዴራሉንና የክልሉን ሕግጋተ መንግስታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

መ/ የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት፣ ሌሎች ልዩ ልዩ ተቋማትና በስሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሠ/ የወረዳው ማኅበራዊ አግልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና ዕቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

ረ/ የወረዳውን ነዋሪ ሕዝብ ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የጸጥታና ፖሊስ ኃይሎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሰ/ ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለወረዳው ምክር

Zonal, other officials and leaders for questioning, and their discharge of responsibilities.

4. The Zonal Council organizes necessary sub-committees for its work.
5. Organizes its own office.

**Article 85**

**The Zonal Council Speakers**

1. The Zonal Council shall be presided by a Speaker and a Deputy Speaker, which is appointed from among the members of the Council on the proposal of the political party or political parties that obtained the majority of votes in the Council;
2. The powers and functions of the Chief and Deputy Speaker of the State Council in this constitution shall apply to the Chief and Deputy Speaker of the Zonal Council as appropriate;

**Article 86**

**Duration and Meeting of the Zonal Council**

1. The duration of the Zonal Council shall be for a term of five years. A new election shall be concluded one month before the end of the Council's term. The new Zonal Council shall begin its work within one month of the end of the

ቤትና ለዞን አስተዳደር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ/ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል፣

ቀ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1፻1 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የወረዳውን ምክር ቤት መሥራች ጉባዔ ይጠራል፣

በ/ በወረዳ ምክር ቤትና ዞን አስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**<u>አንቀጽ ፻3</u>**

**<u>የወረዳ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1 የወረዳው ምክትል ዋና አስተዳደሪዉ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪና ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፡-

ሀ)ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

ለ) በወረዳ ዋና አስተዳዳሪው እና በአስተዳደር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ፡፡

**<u>አንቀጽ ፻4</u>**

**<u>የወረዳ አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት</u>**

1 የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት በዋና አስተዳዳሪው ተመርጠው በሚመደብ አንድ የሥራ ኃላፊ ይመራል፡፡

2 በዚህ ሕገ መንግሥት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት

previous Zonal Council's term.

2. The Zonal Council shall hold at least three regular sessions annually.
3. The presence of two-thirds of the members of the Zonal Council constitutes a quorum. The decision of the Council shall be made by the majority vote of the members.
4. The speaker may call an extra ordinary meeting when the Council is not in regular session. He also obliged to call an extra ordinary meeting at the request of more than one-third of the members.

**Article 87**

**The Zonal Administrative Council**

1. The highest Executive organ of the Zone is the Zonal Administrative Council , and is accountable to the Zonal Chief Administrator, the Zonal Council and the State Executive Council ;
2. The Zonal Administrative Council shall be established consisting of the Chief Administrator, Deputy Administrator and heads of the Zonal Executive departments.
3. Members of the Zonal Administrative Council are collectively responsible for their decisions and

| | |
|---|---|
| የወረዳውን ዋና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በሚመለከት እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ | actions. |
| **ክፍል ሦስት** | **Article 88** |
| **የከተማ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን** | **Powers and Functions of the Zonal Administrative Council** |
| **አንቀጽ ፻5** | The Zonal Administrative Council shall have the following powers and functions: |
| **የከተማ አስተዳደር አደረጃጀት** | 1. Ensure the implementation of State Council and Federal Government bodies laws and decisions in the Zone; |
| 1 በክልሉ የሚገኙ ከተሞች የየራሳቸው አደረጃጀት እና የአስተዳደር ሥርዓት የሚኖራቸው ሆኖ እያንዳንዱ ከተማ አስተዳደር የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡- | 2. Determine the Structure of executive bodies, direct and supervise their work; |
| ሀ/ ምክር ቤት፣ | 3. Draw up Zonal draft budget, submits it to the Zonal Council, and implement up on approval; |
| ለ/ የአስተዳደር ምክር ቤት፣ | 4. Formulate economic and social development policies that are consistant with State policies and strategies; submit it to the Zonal Council and implement same upon approval; |
| ሐ/ የዳኝነት አካል፡፡ | |
